# መጽሐፈ መክብብ

## መግቢያ

### ጸሓፊውና የተጻፈበት ጊዜ

መጽሐፉ መቼ እንደ ተጻፈ ወይም ማን እንደ ጻፈው በመጽሐፉ ውስጥ አልተጠቀሰም፤ ይሁን እንጂ አያሌ የመጽሐፉ ክፍሎች ጸሓፊው ሰሎሞን መሆኑን ያስገነዝባሉ (1፥1:12:16፤ 2፥4-9፤ 7፥26-29፤ 12፥9 ይመ፤ ከ1ነገ2፥9፤ 3፥12፤ 4፥29-34፤ 5፥12፤ 10፥1-8 ጋር ያነጻጽሩ)። በሌላ በኩል ሲታይ ደግሞ የጸሓፊው የማዕረግ ስም፣ "ሰባኪው" መባሉ፣ የዕብራይስጥ ቋንቋ አጻጻፍ ስልቱ፣ ስለ ገዦች ያለው አመለካከት (መሪዎች ፈላጭ ቈራጭ ነገሥታት ከመሆን ይልቅ የአገልጋይ መንፈስ እንዲኖራቸው ሐሳብ መሰንዘሩ፣ ለዚሁም 4፥1-2፤ 5፥8-9፤ 8፥2-4፤ 10፥20 ይመ)፣ ጸሓፊው ሌላ ሰው መሆኑንና የተጻፈበት ዘመንም ከሰሎሞን ዘመን በኋላ መሆኑን ሊያመለክት ይችላል።

### ዐላማና ስልቱ

ጸሓፊው በረጅም ዕድሜው ባለፈበትና ከልደት እስከ ሞት ባገኘው የሕይወት ገጠመኝ መሠረት ጥቅሉን ዓለም ይመዝናል፤ ከሞት ባሻገር ያለው አድማስ ግን ምን እንደሚመስል በትክክል ማስተዋል ለማንም ፍጡር የሚቻል አይደለም። ዓለም ራሷ ዐቢይ ምስጢር ናት፤ ከሁሉም ውስብስብ የሆነው ምስጢር ግን ሰው ራሱ ነው።

በዚህ መጽሐፍ ላይ "ሰባኪው" የተባለው ሰው፣ ከራሱ ግንዛቤ አኳያ የሰውን ችሎታ ሚዛን ላይ በማስቀመጥ ይለካል። ሌላው ቀርቶ የእግዚአብሔር ሰው ነው የተባለው ጥበብ እንኳ ውሱን መሆኑን ያስተውላል (1፥13:16-18፤ 7፥24፤ 8፥16-17)፤ ይህ የሰው ጥበብ የእግዚአብሔርን ዐቢይ ዕቅድ መርምሮ ሊያውቅ አይችልም፤ የሰውን የእስከ ወዲያኛው ትርጒም በወጉ ለመረዳት ብቃት የለውም። ጸሓፊው የሰውን ዘር ጥረት ሲመለከት፣ እስኪታክተው ድረስ አንድን ነገር ለመጨበጥ ይዋከባል፤ የተመኘውን እጁ ካደረገ በኋላ ደግሞ በአሻጋሪ ሲያየው የሚያማልለውንና ገንዘብ ያላደረገውን ነገር ለመያዝ ይጣደፋል። ዓለም በጓዳዋ ሸሽጋ የያዘችውን ምስጢር እስከተቻለው ፈልፍሎ ያወጣል፤ መሠረታዊ መዋቅሯን ለመለወጥ ይሞክራል፤ የሰውን ዘር የውሱንነት ዐጥር አፍርሶ፣ የራሱን ዕድል የወሰነ ይመስለዋል። የሰው ዘር ተስፋዬና ምኞቴ ነው የሚለውን ጒዳይ በጽኑ መንፈስ አጥብቆ የያዘው ይምሰለው እንጂ፣ በሰባኪው ዐይን በትክክል ሲታይ ግን፣ ትርጒም የለሽና ነፋስን የመከተል ያህል ነው (1፥14፤ 2፥11:17:26፤ 4፥4:16፤ 6፥9 ይመ፤ ከ1፥17፤ 4፥6 ጋር ያነጻጽሩ)።

እግዚአብሔር እንደ በጎ ፈቃዱ ለራሱ ዐላማ ሁሉንም ነገር የፈጠረና ያበጀ መሆኑን ያስተማረው ሌላ ሳይሆን እምነት ነው (3፥1-15፤ 5፥19፤ 6፥1-2፤ 9፥1 ይመ)። የሰው ድርሻ ከላይ የተመለከተውን የመለኮት በጎ ፈቃድም ሆነ የራሱን ውሱንነት እግዚአብሔር ዐውቆ ያዘጋጀው መሆኑን አምኖ መቀበል ነው። እንግዲህ የሰው ዘር የዓለምንና የራሱን ምንነት በትዕግሥት በማስተዋል፣ እግዚአብሔር ፈቅዶ በወሰነለት ዓለምና ሕይወት በሐሤት መኖር ይገባዋል፤ ራሱን ተጨባጭ ላልሆነ ነገር ሳይዳርግ ዐቅሙን ማወቅ ይኖርበታል። በማንኛውም ረገድ ጥንቁቅ ሆኖ እንዲኖር ግድ ነው፤ በእግዚአብሔርና እግዚአብሔር በሰጠው ንጉሥ ፊት በአክብሮት እንዲጓዝ ይጠበቅበታል፤ ከሁሉም በላይ ግን እግዚአብሔርን ፈርቶና ሕጉን አክብሮ ሊኖር ይገባል (12፥13)።

### አስተምህሮው

የእግዚአብሔርን ጒዳይ ዐቢይ ቁም ነገር አድርጎ ያልያዘ ሕይወት ዐላማ ቢስና ትርጒም የለሽ ነው፤ እግዚአብሔር የሌለበት ሕይወት፣ ምንም ነገር ሊያረካው አይችልም (2፥25)፤ እግዚአብሔር እንደ ቸርነቱ የሚገኝበት ሕይወት፣ እርሱ የሚሰጠውን በጎ ነገርና በሕይወት ውስጥ እውን ሆኖ ያለውን ሁሉ በምስጋና እንዲቀበል (ያዕ1፥17)፣ እርሱ በሰጠውም ጸጋ መጠቀምና ሐሤት ማድረግ ይገባል (2፥26፤ 11፥8)። ይህ መጽሐፍ የአንድን አዛውንት ፍልስፍናና ሥነ መለኮታዊ አመለካከት ያሳያል (12፥1-7)፤ የአዛውንቱ አያሌ የሕይወት ጒዞም በአብዛኛው እግዚአብሔርን መሠረት ያላደረገ በመሆኑ፣ በእነዚያ ጊዜያት ሕይወት ትርጒም አልባ ሆኖበት ነበር።

### አስተዋፅኦ

1. ጸሓፊው (1፥1)
2. መሪ ሐሳብ፤ እግዚአብሔር ያልባረከው የሰው ጥረት እርባና ቢስ መሆኑ (1፥2)
3. መግቢያ፤ ርካታ ለማግኘት ሲባል ሀብት ለማጠራቀም የሚደረገው መዋተት ፍሬ ቢስ ነው (1፥3-11)።
4. ሐተታ ክፍል 1፤ በገሃድ እንደሚታየው ሕይወት እጅግ ምስጢርና ትርጒም አልባ ብትሆንም እንኳ፣ የእግዚአብሔር ስጦታ በመሆኗ በእርሷ ርካታ ማግኘት ተገቢ ነው (1፥12-11፥6)
5. ሐተታ ክፍል 2፤ እርጅናና ሞት ገሥግሠው መምጣታቸው ስለማይቀር፣ የሰው ዘር በአፍላ ዘመኑ ሳለ በማንኛውም ረገድ ሐሤት ያደርግ ዘንድ ተገቢ ነው፤ ሐሤት ሲያደርግም የእግዚአብሔር ፍርድ የማይቀር መሆኑን ልብ ማለት ይገባዋል (11፥7-12፥7)
6. መሪ ሐሳብ በድጋሚ (12፥8)
7. መደምደሚያ፤ በፍርሀትና በአክብሮት እግዚአብሔርን ማመንና ትእዛዙን መፈጸም (12፥9-14)

## ሁሉም ነገር ከንቱ ነው

1 በኢየሩሳሌም የነገሠው፣ የዳዊት
ልጅ፣ የሰባኪው ቃል[ሀ]፤
2 ሰባኪው፣
"ከንቱ፣ ከንቱ፣
የከንቱ ከንቱ፤
ሁሉም ነገር ከንቱ ነው" ይላል።
3 ከፀሐይ በታች ከሚለፋበት ተግባር ሁሉ፣
ሰው ምን ትርፍ ያገኛል?
4 ትውልድ ይሄዳል፤ ትውልድ ይመጣል፤
ምድር ግን ለዘላለም ጸንታ ትኖራለች።
5 ፀሐይ ትወጣለች፤ ትጠልቃለችም፤
ወደምትወጣበትም ለመመለስ ትጣደፋለች።
6 ነፋስ ወደ ደቡብ ይነፍሳል፤
ወደ ሰሜንም ይመለሳል፤
ዞሮ ዞሮ ይሄዳል፤
ዘወትርም ወደ ዑደቱ ይመለሳል።
7 ወንዞች ሁሉ ወደ ባሕር ይፈሳሉ፤
ባሕሩ ግን ፈጽሞ አይሞላም፤
ወንዞች ወደ መጡበት ስፍራ፣
ወደዚያ እንደ ገና ይመለሳሉ።
8 ሰው መናገር ከሚችለው በላይ፣
ነገሮች ሁሉ አድካሚ ናቸው፤
ዐይን ከማየት አይጠግብም፤
ጆሮም በመስማት አይሞላም።
9 የነበረው ነገር እንደ ገና ይሆናል፤
የተደረገውም ተመልሶ ይደረጋል፤
ከፀሐይ በታች ምንም አዲስ ነገር የለም።
10 ማንንም፣ "እነሆ፤ ይህ አዲስ ነገር ነው!"
ሊል የሚችለው አንዳች ነገር አለን?
ቀድሞውኑ በዚሁ የነበረ ነው፤
ከእኛ በፊት የሆነ ነው።
11 የቀድሞ ነገሮች መታሰቢያ የላቸውም፤
ወደ ፊት የሚመጡትም ቢሆኑ፣
ከእነርሱ በኋላ በሚተኩት፣
አይታወሱም።

## ጥበብ ከንቱ ነው

12 እኔ ሰባኪው፣ በኢየሩሳሌም የእስራኤል
ንጉሥ ነበርሁ። 13 ከሰማይ በታች የተደረገውን
ሁሉ በጥበብ ለማጥናትና ለመመርመር ራሴን
አተጋሁ፤ ስምላክ በሰዎች ላይ የጫነው
እንዴት ያለ ከባድ ሸክም ነው! 14 ከፀሐይ
በታች የተደረገውን ነገር ሁሉ አየሁ፤ ሁሉም
ከንቱ፣ ነፋስንም እንደ መከተል ነው።
15 የተጣመመው ሊቃና አይችልም፤
የሌለም ነገር ሊቈጠር አይችልም።
16 እኔም በልቤ፣ "እነሆ፤ ከእኔ በፊት
በኢየሩሳሌም ከገዙት ከማንኛቸውም ይልቅ
ታላቅ ሆኛለሁ፤ ጥበብም በዝቶልኛል፤ በብዙ
ጥበብና ዕውቀት ተመክሮም ዐልፌአለሁ"
አልሁ።

1፥1 ቍ12፤ምሳ1፥1፤መክ7፥27፤12፥10
1፥2 መዝ39፥5-6፤62፥9፤መክ12፥8፤ሮሜ 8፥20-21
1፥3 መክ2፥11:22፤3፥9፤5፥15-16
1፥4 ኢዮ 8፥19
1፥5 መዝ19፥5-6
1፥7 ኢዮ 36፥28
1፥8 ምሳ 27፥20
1፥9 መክ 2፥12፤3፥15
1፥11 ዘፍ40፥23፤መዝ88፥12፤መክ2፥16፤8፥10፤9፥5:15
1፥12 ቍ1መክ2፥9
1፥13 ዘፍ3፥17፤ኢዮ 28፥3፤መክ3፥10
1፥14 መክ2፥11:17፤4፥4፤6፥9
1፥15 መክ7፥13
1፥16 1ነገ3፥12

[ሀ]1 ወይም *የጉባኤ መሪ* እንዲሁም በቍ2 እና 12

1፥1 ሰባኪው፤ የጥበብ አስተማሪ ነው (12፥9)፤ ቍ2 እና 12 ላይም ተደግሞአል። የዕብራይስጡ አባባል "ጉባኤ" ለሚለው ከተሰጠው ቃል ጋር የተዛመደ ነው (ዘፀ16፥3፤ ዘኍ16፥3 ይመ)፤ በ12፥9-10 ላይ ተግባሩ የተገለጸው ሰባኪ በጉባኤውም ውስጥ ኀላፊነት ሳይኖረው አይቀርም። ሰሎሞን ራሱን ለማመልከት በተደጋጋሚ በዚህ የቅጽል ስም ይጠቀማል፤ ይህም ጉባኤውን የሚጠራና ንግግር የሚያደርግ እርሱ እንደ ሆነ ያሳያል፤ የሚናገረውም በጥንቷ እስራኤል እግዚአብሔር የራሱን እውነት ለሰዎች ለማስተላለፍ ይጠቀምበት ለነበረው የጠቢባን ጉባኤ ነው (ኤር 18፥18)። ***የዳዊት ልጅ፤*** በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስሙ ባይጠቀስም፣ ሰሎሞንን ያመለክታል። "ልጅ" የሚለው ቃል በዕብራይስጥ ወደ ኋላ ያለውን አንድ ትውልድ ወይም ብዙ ትውልድ ወይም በሌላው እግር የሚተካውን ሰው ሊያሳይ ይችላል (ዘፍ 4፥21፤ ይመ፤ እንዲሁም ከዚህ መጽሐፍ መግቢያ "ጸሐፊውና የተጻፈበት ጊዜ" የሚለውን ይመ)።

1፥2፤ የጸሐፊውን መሪ ሐሳብ በአጭሩ ይገልጻል (12፥8 ይመ)። *ከንቱ፤* ይህ ቍልፍ ቃል በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ሠላሳ አምስት ጊዜ የተጠቀሰ ሲሆን፣ በሌላ ቦታ አንዴ ብቻ ተጠቅሶአል (ኢዮ 27፥12) ቃሉ በዕብራይስጥ "ነፍስ" የሚል ትርጕም አለው (መዝ39፥5:11፤ 62፥9፤ 144፥4 ይመ)። የመጽሐፉ መሠረታዊ መልእክት፣ ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ግንኙነት የሌለው ሕይወት ትርጕም አልባ፣ የማይረባ፣ ባዶ፣ ዋጋ ቢስና ከንቱ መሆኑን የሚያመለክት ነው። ሕይወት ዋጋ ያለው የሚሆነው በእግዚአብሔርና በቃሉ ላይ የተመሠረተ ሲሆን ብቻ ነው። *ሁሉም ነገር፤* ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ ሰው የሚያደርገው ማንኛውም ነገር ማለት ነው፤ ቍ 8 ይመ።

*1፥3-11፤* በዚህ ክፍል ጸሐፊው የሰው ጥረት ፋይዳ ቢስና ውጤት የሌለው መሆኑን በመናገር የመልእክቱን መሪ ሐሳብ ያብራራል።

1፥3 *ምን ትርፍ፤* የሰው ድካም መልካም ውጤት ያለው ለመሆኑ ዋስትና የሚሰጥ ነገር የለም። *ከፀሐይ በታች፤* በመጽሐፉ ውስጥ ከሚገኙት ቍልፍ ሐረጎች አንዱ ይህ ነው፤ ይህች ዓለም የምትሰጠው ነገር ውስን መሆኑን ያመለክታል። "ከሰማይ በታች" (ቍ13፤2፥3፥3፥1) የሚለውም ብዙ ጊዜ የተደጋገመ ባይሆንም፣ ዐልፎ ዐልፎ የተጠቀሰ ተመሳሳይ ሐረግ ነው።

1፥4 *ምድር ... ለዘላለም ጸንታ ትኖራለች፤* በአንጻሩ የሰው የሕይወት ዘመን እንደ ጥላ ፈጥኖ የሚያልፍ ነው (መዝ 144፥4)።

1፥8 *ነገሮች ሁሉ፤* በቍ 4-7 የተጠቀሰው ማንኛውም ነገር ማለት ነው (የቍ 2 ማብ ይመ)።

1፥10 *አዲስ ነገር፤* ያለፈው ሁኔታ በቀላሉና በፍጥነት ስለሚረሳ፣ ብዙ ነገር አዲስ ይመስላል፤ አሮጌውም ነገር መልኩን ቀይሮ አዲስ ልብስ ለብሶ ይመጣል።

*1፥12-18፤* ሰው የሚያደርገው ሁሉ ከንቱ እንደ ሆነ በሚገልጸው በዚህ መሪ ሐሳብ (በተለይ ቍ 3:11 ይመ)፣ ጸሐፊው የሰው ልፋትና (ቍ 12-15፤ ከ2፥1-11 ጋር ያነጻጽሩ) ምድራዊ ጥበብን መከተል ሁለቱም (ቍ 16-18፤ ከ2፥12-17 ጋር ያነጻጽሩ) ዋጋ ቢስና ትርጕም የለሽ መሆናቸውን ያመለክታል።

1፥12 *እኔ፤* ጸሐፊው በአንደኛ መደብ ተውላጠ ስም ከተጠቀመ በኋላ በመጨረሻ ወደ ሦስተኛ መደብ ተውላጠ ስም ይመለሳል (12፥9-14)።

1፥13 *አምላክ፤* ጸሐፊው እግዚአብሔር ለማለት የተጠቀመበት የዕብራይስጥ ቃል 'ኤሎሂም' የሚለውን ስም ብቻ ሲሆን፣ ቃሉ ሠላሳ ጊዜ ያህል በመጽሐፉ ተጠቅሶአል፤ ይህም የእግዚአብሔርን ፍጹም ታላቅነት የሚገልጽ ቃል ነው። ያህዌ (እግዚአብሔር) የሚለውን የኪዳን ስሙን (የዘፀ 3፥15 ማብ ይመ) አልተጠቀመበትም።

1፥14 *ነፋስን እንደ መከተል፤* ከንቱና ትርጕም የለሽ መሆኑን የሚያሳይ ሥዕላዊ አገላለጽ ነው (ከመጽሐፉ መግቢያ "ዐላማና ስልቱ" የሚለውን ይመ)። እነዚህ ቃሎች በመጽሐፉ ውስጥ በተደጋጋሚ ተጠቅሰዋል (እዚህ ላይና ቍ17፤2፥11:17:26፤ 4፥4: 6:16፤ 6፥9፤ እንዲሁም 5፥16 ይመ)።

*1፥15፤* 7፥13 እና ማብ ይመ። ከሁኔታዎች አለመለወጥ የተነሣ፣ የሰው ጥረት ከንቱ ነው፤ ተስፋም አይጣልበትም፤ ስለዚህ አስተማሪው በመጨረሻ እንደሚመክረው፣ ማንኛውንም ነገር እንዳለ በደስታ መቀበልንና በሕይወት ጕዞ ውስጥ በእግዚአብሔር የተመደበልንን ዕጣ ፈንታ መልመድ ይገባናል።

1፥16 *ከእኔ በፊት በኢየሩሳሌም ከገዙት፤* 2፥7:9 ይመ። ይህ አባባል ንጉሥ ሰሎሞንን እንዲሁም ከዳዊት በፊት የነበሩትን ነገሥታት ማለትም መልከ ጼዴቅ (ዘፍ 14፥18)፣ አዶኒጼዴቅ (ኢሱ 10፥1) እና አብዲ ከፋ (ከግብፅ በተጻፉት የአማርና ደብዳቤዎች ውስጥ ተጠቅሶአል) የመሳሰሉትን ሊመለከት ይችላል።

[17]ከዚያም የጥበብንና የእብደትን፣ የሞኝነት
ንም ነገር ለመገንዘብ ራሴን አተጋሁ፤ ይህም
ነፋስን እንደ መከተል መሆኑን ተረዳሁ።

[18]ጥበብ ሲበዛ፣ ትካዜ ይበዛልና፤
ዕውቀት ሲጨምርም ሐዘን ይበዛል።

**ምድራዊ ደስታ ከንቱ ነው**

**2** እኔም በልቤ፣ "መልካም የሆነውን ለማ
ወቅ፣ በተድላ ደስታ እፈትንሃለሁ"
አልሁ፤ ነገር ግን ያም ከንቱ ነበረ። [2]ደግሞም፣
"ሣቅ ሞኝነት ነው፤ ተድላ ደስታስ ምን ይጠ
ቅማል?" አልሁ። [3]አሁንም አእምሮዬ በጥበብ
እየመራኝ ራሴን በወይን ጠጅ ደስ ለማሰ
ኘት፣ ሞኝነትንም ለመያዝ ሞከርሁ፤ ሰዎች
በአጭር የሕይወት ዘመናቸው ከሰማይ በታች
ባለው ላይ ቢሠሩት ሊጠቅማቸው የሚችል
ምን እንደ ሆነ ለማየት ፈለግሁ።
[4]ታላላቅ ነገሮችን አከናወንሁ፤ ለራሴ
ቤቶችን ሠራሁ፤ ወይንንም ተከልሁ፤ [5]አትክ
ልትን ተከልሁ፤ የመዝናኛ ስፍራዎችን አዘ
ጋጀሁ፤ በእነዚህም ላይ ፍሬ የሚያፈሩ የዛፍ
ዐይነቶችን ሁሉ ተከልሁባቸው፤ [6]የሚለመ
ልሙ ዛፎችን ለቦይ የሚሆኑ የውሃ ማጠራቀ
ሚያዎችን ሠራሁ። [7]ወንድና ሴት ባሪያዎችን
ገዛሁ፤ በቤቴም የተወለዱ ሌሎች ባሪያዎች
ነበሩኝ። ከእኔ በፊት በኢየሩሳሌም ከነበሩት
ይልቅ ብዙ የከብት፣ የበግና የፍየል መንጋ
ዎች ነበሩኝ። [8]ለራሴም ብርንና ወርቅን፣
የነገሥታትና የአውራጃዎችን ሀብት አካበ
ትሁ፤ ወንድና ሴት አዝማሪዎች፣ የሰው
መደሰቻ የሆኑ ቅምጦች[a] ነበሩኝ። [9]ከእኔ
በፊት በኢየሩሳሌም ከነበሩት ሁሉ ይልቅ
እጅግ ታላቅ ሆንሁ፤ በዚህ ሁሉ ጥበቤ
ከእኔ ጋር ነበረች።

[10]ዐይኔ የፈለገውን ሁሉ አልከለከልሁትም፤
ለልቤም ምድራዊ ደስታን አልነፈግሁትም፤
ልቤ በሠራሁት ሁሉ ደስ አለው፤
ይህም የድካሜ ሁሉ ዋጋ ነበረ።
[11]ሆኖም እጆቼ የሠሩትን ሁሉ፣
ለማግኘትም የደከምሁትን ድካም ሁሉ
ሳስብ፣
ሁሉም ከንቱ፣ ነፋስንም እንደ መከተል
ነበር፤
ከፀሐይ በታች ምንም ትርፍ አልነበረም።

1፥17 መክ7፥23፤ 8፥16፤መክ2፥3:12፤ 7፥25
1፥18 መክ2፥23፤ 12፥12፤ኤር45፥3
2፥1 ቍ 24፤ መክ7፥4፤8፥15
2፥2 ምሳ14፥13
2፥3 ቍ 24-25፤መሳ 9፥13፤ሩት3፥3፤መክ 1፥17፤3፥12-13፤5፥18 ፤8፥15
2፥4 2ዜና 2፥1፤ 8፥1-6፤ማሕ8፥11
2፥7 2ዜና 8፥7-8
2፥8 መሳ3፥15፤ 2ሳሙ 19፥35፤ 1ነገ9፥28
2፥9 1ዜና29፥25፤ መክ1፥12
2፥11 መክ1፥3:14
2፥12 መክ1፥9:17
2፥13 መክ7፥11-12 :19፤9፥18
2፥14 መዝ49፥10፤ መክ3፥19፤6፥6፤7፥2፤ 9፥3:11-12
2፥15 ቍ 19፤ መክ6፥8
2፥16 መዝ49፥10፤ 112፥6፤መክ1፥11
2፥17 መክ1፥14
2፥18 መዝ39፥6፤ 49፥10
2፥19 ቍ 15

**ጥበብና ሞኝነት ከንቱ ናቸው**

[12]ከዚያም ጥበብን፣
እብደትንና ሞኝነትን ለመመርመር
ሐሳቤን መለስሁ፤
አስቀድሞ ከተደረገው በቀር፣
ከንጉሡ በኋላ የሚመጣው ሰው ምን
ሊያደርግ ይችላል?
[13]ብርሃን ከጨለማ እንደሚበልጥ ሁሉ፣
ጥበብም ከሞኝነት እንደሚበልጥ
ተመለከትሁ።
[14]የጠቢብ ሰው ዐይኖች ያሉት በራሱ
ውስጥ ነው፤
ሞኝ ግን በጨለማ ውስጥ ይራመዳል፤
ሆኖም የሁለቱም ዕድል ፈንታ፣
አንድ መሆኑን ተገነዘብሁ።
[15]ከዚያም በልቤ፣
"የሞኙ ዕድል ፈንታ በእኔም ላይ ይደርሳል፤
ታዲያ ጠቢብ በመሆኔ ትርፌ ምንድን ነው?"
አልሁ።
በልቤም፣ "ይህም ደግሞ ከንቱ
ነው" አልሁ።
[16]ጠቢቡም ሰው እንደ ሞኙ ለዘላለም
አይታወስምና፤
በሚመጡት ዘመናት ሁለቱም ይረሳሉ።
ለካ፣ ጠቢቡም እንደ ሞኙ መሞቱ
አይቀርም!

**ጥረት ከንቱ ነው**

[17]ስለዚህ ከፀሐይ በታች የሚሠራው ሥራ
አሳዛኝ ስለ ሆነብኝ ሕይወትን ጠላሁ፤ ይህም
ሁሉ ከንቱ፣ ነፋስንም እንደ መከተል ነው።
[18]ከፀሐይ በታች የደከምሁበትን ነገር ሁሉ
ጠላሁት፣ ከኋላዬ ለሚመጣው የግድ እተ
ውለታለሁና። [19]እርሱ ጠቢብ ወይም ሞኝ
ይሆን እንደ ሆነ ማን ያውቃል? ሆኖም ከፀሐይ
በታች ድካሜንና ችሎታዬን ባፈሰስሁበት
ሥራ ሁሉ ላይ ባለቤት ይሆንበታል፤ ይህም
ደግሞ ከንቱ ነው። [20]ስለዚህ ከፀሐይ በታች
በደከምሁበት ነገር ሁሉ ላይ ልቤ ተስፋ
መቍረጥ ጀመረ፤ [21]ምክንያቱም ሰው ሥራ
ውን በጥበብ፣ በዕውቀትና በብልኀት ሠርቶ፣
ከዚያ ያለውን ሁሉ ለሌላ ላልለፋበት ሰው
ይተውለታል። ይህም ደግሞ ከንቱና ትልቅ

[a]8 በዕብራይስጥ የዚህ ሐረግ ትርጕም አይታወቅም

*1፥18፤* ከእግዚአብሔር ያልሆነ ጥበብ ሁሉ ወደ ሐዘን ይመራል።
*2፥1-11፤* በዚህ ክፍል ሰባኪው ደስታ ብቻውን ለሕይወት ትርጕም ወይም ርካታን ሊሰጥ እንደማይችል ይገልጻል (1፥12-15 እንዲሁም የ1፥12-18 ማብ ይመ)።
2፥1 *በልቤ ... አልሁ፤* ቍ 15፤1፥16 ይመ።
2፥3 *አእምሮዬ በጥበብ እየመራኝ፤* ጸሓፊው መልካም የሆነውን (ቍ1) እና የሚጠቅመውን (ቍ3) ለማወቅ፣ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ (ቍ9) በጥበብ ተጠቅሞአል።
*2፥4-9፤* ስለ ሰሎሞን ዝናና ስለ ነበሩት ሚስቶች የሚናገረውን 1ነገ 4-11 ይመ።
2፥10 *በሠራሁት /... የድካሜ፤* እነዚህ ቃላት በመጽሐፈ መክብብ ውስጥ ከሃያ አምስት ጊዜ በላይ የተጠቀሱ ሲሆን፣ እግዚአብሔር የሌለበት ሥራ፣ ድካምና ልፋት ከንቱ (ቍ11) መሆናቸውን የሚያመለክቱ ናቸው።
*2፥12-17፤* በሰው ጥበብ እርካታን ለማግኘት መሞከር ሞኝነት እንደ ሆነ ሰባኪው በድጋሚ ይገልጻል (1፥16-18፤ እንዲሁም የ1፥12-18 ማብ ይመ)።
2፥13 *ጥበብ ከሞኝነት እንደሚበልጥ፤* የዓለም ጥበብ እንኳ ከሞኝነት ይሻላል፤ ነገር ግን የጥበበኞችና የሞኝ ሰው ዕጣ ፈንታ አንድ ስለ ሆነ፣ በመጨረሻ ጥበብም ቢሆን ፋይዳቢስ ነው (ቍ 14፤ መዝ 49፥10 ይመ)።
2፥14 *ዐይኖች፤* መልካሙንና ክፉውን ለይቶ የመረዳት ችሎታን ያመለክታል።
*2፥16፤* ታላቅና ዝነኛ የተባለው መሪ እንኳ ቢሆን፣ በሰዎች ዘንድ ቶሎ የሚረሳ ይሆናል (1፥11 ይመ)።
2፥18 *ከኋላዬ ለሚመጣው ... እተውለታለሁና፤* ቍ21፤ መዝ 39፥6፤ ሉቃ 12፥20 ይመ።
2፥19 *ማን ያውቃል?* ዓለማዊ ሰው፣ "ማን ያውቃል?" በማለት የሚያነሣውን የበለጠ አመራማሪ ጕዳይ በ3፥21 ይመ።

ጒዳት ነው። 22ሰው ከፀሓይ በታች በሚደ
ክምበት ጥረትና ልፋት ሁሉ ትርፉ ምንድን
ነው? 23በዘመኑ ሁሉ ሥራው ሥቃይና ሐዘን
ነው፤ በሌሊትም እንኳ ቢሆን አእምሮው
አያርፍም። ይህም ደግሞ ከንቱ ነው።
24ለሰው ከመብላትና ከመጠጣት፣ በሥራ
ውም ከመርካት ሌላ የሚሻለው ነገር የለውም፤
ይህም ደግሞ ከእግዚአብሔር እጅ እንደሚሰጥ
አየሁ፤ 25ከእርሱ ዘንድ ካልሆነ ማን መብላትና
መደሰት ይችላል? 26እግዚአብሔር፣ ደስ ለሚ
ያሰኘው ሰው ጥበብን፣ ዕውቀትንና ደስታን
ይሰጠዋል። ለኀጢአተኛ ግን፣ እግዚአብሔርን
ደስ ለሚያሰኘው ይተውለት ዘንድ፣ ሀብትን
የመሰብሰብና የማከማቸት ተግባር ይሰጠዋል።
ይህም ከንቱ፣ ነፋስንም እንደ መከተል ነው።

## ለሁሉም ጊዜ አለው

3 ለሁሉም ነገር ጊዜ አለው፤
ከሰማይ በታች ለሚከናወነው
ለማንኛውም ነገር ወቅት አለው፤
2ለመወለድ ጊዜ አለው፤ ለመሞትም
ጊዜ አለው፤
ለመትከል ጊዜ አለው፤ ለመንቀልም
ጊዜ አለው፤
3ለመግደል ጊዜ አለው፤ ለማዳንም
ጊዜ አለው፤
ለማፍረስ ጊዜ አለው፤ ለመገንባትም
ጊዜ አለው፤
4ለማልቀስ ጊዜ አለው፤ ለመሣቅም
ጊዜ አለው፤
ለሐዘን ጊዜ አለው፤ ለጭፈራም
ጊዜ አለው፤
5ድንጋይ ለመጣል ጊዜ አለው፤ ድንጋይ
ለመሰብሰብም ጊዜ አለው፤
ለመተቃቀፍ ጊዜ አለው፤ ለመለያየትም
ጊዜ አለው፤
6ለመፈለግ ጊዜ አለው፤ ለመተው
ጊዜ አለው፤
ለማስቀመጥ ጊዜ አለው፤ አውጥቶ
ለመጣልም ጊዜ አለው፤
7ለመቅደድ ጊዜ አለው፤ ለመስፋትም

2፥22 መክ 1፥3
2፥23 ዘፍ3፥17፤
ኢዮ7፥2፤ መክ1፥18
2፥24 ቊ1:3፤ኢዮ
2፥10፤መክ3፥12-13
፤22፤5፥17-19፤
7፥14፤9፥7-10፤
11፥7-10
2፥25 መዝ127፥2
2፥26 ኢዮ 9፥4፤
27፥17፤ምሳ13፥22
3፥1 ቊ11:17፤
መክ8፥6
3፥2 ኢሳ28፥24
3፥3 ዘዳ5፥17
3፥7 አስ4፥14
3፥9 መክ1፥3
3፥10 መክ1፥13
3፥11 ቊ1፤
ኢዮ11፥7፤
28፥23፤ሮሜ11፥33
3፥13 ዘዳ12፥7:18፤
መዝ34፥12፤
መክ2፥3:24
3፥14 ኢዮ23፥15፤
መክ5፥7፤7፥18፤
8፥12-13
3፥15 መክ1፥9፤
6፥10
3፥17 ቊ1፤
ኢዮ19፥29፤
መክ11፥9፤12፥14
3፥18 መዝ73፥22

ጊዜ አለው፤
ለዝምታ ጊዜ አለው፤ ለመናገርም ጊዜ
አለው፤
8ለመውደድ ጊዜ አለው፤ ለመጥላትም
ጊዜ አለው፤
ለጦርነት ጊዜ አለው፤ ለሰላምም ጊዜ
አለው።

9ሠራተኛ ከጥረቱ የሚያገኘው ትርፍ ምንድን
ነው? 10ሰዎች ይደክሙበት ዘንድ እግዚአብሔር
የሰጣቸውን ከባድ የሥራ ጫና አየሁ። 11ሁሉ
ንም ነገር በጊዜው ውብ አድርጎ ሠራው፤
በሰዎችም ልብ ዘላለማዊነትን አኖረ፤ ይሁን
እንጂ እግዚአብሔር ከመጀመሪያ እስከ መጨ
ረሻ ያደረገውን ማወቅ አይችሉም። 12ለሰ
ዎች፣ በሕይወት እያሉ ደስ ከመሰኘትና
መልካምን ነገር ከማድረግ የተሻለ ነገር እን
ደሌለ ዐወቅሁ። 13ሰው ሁሉ ይበላና ይጠ
ጣ ዘንድ፣ በሚደክምበትም ሁሉ ርካታን
ያገኝ ዘንድ ይህ የእግዚአብሔር ችሮታ ነው።
14እግዚአብሔር ያደረገው ሁሉ ለዘላለም እንደሚ
ኖር ዐውቃለሁ፤ በእርሱ ላይ ምንም አይጨ
መርም፤ ከእርሱም ምንም አይቀነስም፤ ሰዎች
ያከብሩት ዘንድ ይህን አደረገ።

15አሁን ያለው ከዚህ በፊት የነበረው ነው፤
ወደፊት የሚሆነውም ቀድሞ የነበረ ነው፤
እግዚአብሔርም ያለፈውን መልሶ ይሻዋል*።

16ከፀሓይ በታችም ሌላ ነገር አየሁ፤

በፍርድ ቦታ ዐመፅ ነበር፤
በፍትሕ ቦታ ግፍ ነበር።

17እኔም በልቤ "ለማንኛውም ድርጊት፣
ለማንኛውም ተግባር ጊዜ ስላለው፣
እግዚአብሔር ጻድቁንና ኀጢአተኛውን
ወደ ፍርድ ያመጣቸዋል" ብዬ አሰብሁ።

18እንዲህም ብዬ አሰብሁ፤ "ሰዎች፣ እንደ
እንስሳት መሆናቸውን ያዩ ዘንድ እግዚአብሔር
ይፈትናቸዋል። 19የሰው ዕድል ፈንታ እንደ እን
ስሳት ነው፤ ሁለቱም ዕጣ ፈንታቸው አንድ

*15 ወይም እግዚአብሔር ያለፈውን መልሶ ይጠራዋል

*2፥24-25፤* የመክብብ መጽሐፍ መሪ ሐሳብ ሲሆን፣ በ3፥12-13:22፤5፥18-20፤8፥15፤9፥7 ላይ ተደጋግሞ ተጠቅሶአል፤ በ12፥13 ላይም የሐሳቡ ማጠቃለያ የሆነው ዋና ነገር ተመልክቶአል። ሕይወት ትርጒም ሊኖረውና እውነተኛ ደስታ ሊገኝበት የሚችለው፣ በእግዚአብሔር ብቻ ነው፤ ከእርሱ ውጭ ምንም የሚያረካ ነገር የለም፤ በእርሱ ግን ርካታና ደስታ እናገኛለን። እግዚአብሔርን ስናውቅና እርሱን ስናከብር፣ እውነተኛ ደስታ እናገኛለን (12፥13)።

2፥26 *ለኀጢአተኛ ግን፤* ይህን ልዩ መርሕ በበለጠ ለመረዳት በ8፥14 እና በመዝ 73፥1-12 ላይ ያለውን ይመ።

*3፥1-22፤* በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ልንቈጣጠረው በማ ይቻለን በጊዜና በለውጥ ቊጥጥር ሥር መሆናችንን ሰባኪው ያመለክታል፤ ይህንም ሁኔታ ከእግዚአብሔር ዘላለማዊነትና ታላቅነት ጋር ያነጻጽራል። እግዚአብሔር በኀያልነቱ የሕይወትን አካሄድ ሁሉ አስቀድሞ ያውቃል (ለምሳሌ የቊ2-8:14 ተቃራኒዎች)።

*3፥1፤* ከ8፥6 *ጋር ያነጻጽሩ።*

3፥2 *ጊዜ፤* በእግዚአብሔር የተወሰነ ጊዜ ነው (መዝ 31፥15፤ ምሳ 16፥1-9 ይመ)።

*3፥11፤* የምዕራፉን ማጠቃለያ ሐሳብ የያዘ ነው፤ ይኸውም፣ ውብ የሆነው ነገር ግን ከማጓጓት በስተቀር የማይጨበጠው የእግዚአብሔር ዓለም ምንነት ከማስተዋል በላይ ቢሆንም፣ የሚሰጠው ርካታ እጅግ አነስተኛ መሆኑን ያመለክታል። እኛ የተፈጠርነው ለዘላለም ለመኖር ስለ ሆነ፣ ጊዜያዊ የሆነው ነገር ሙሉና ዘላቂ ርካታ ሊሰጠን አይችልም።

*3፥12-13፤* የመጽሐፉን መደምደሚያ ሐሳብ የሚያመለክት ነው። ለእግዚአብሔር ሰዎች ሕይወት ትርጒም ሊሰጣቸው የሚችለው ከእግዚአብሔር እጅ በደስታ ሲቀበሉት ብቻ ነው።

3፥14 *ለዘላለም፤* ይህ ቃል በቊ11 ላይ የተጠቀሰውን ተመሳሳይ አባባል ("ዘላለማዊነትን") የበለጠ ግልጽ ያደርገዋል። *ያከብሩት፤* የመጽሐፉ መልእክት ማጠቃለያ ሐሳብ ነው (ከ12፥13 ጋር ያነጻጽሩ)።

*3፥15፤* 1፥9 *ይመ።*

3፥17 *ፍርድ፤* ፍትሕን በማጣመም ወይም በአድልዎ በሰዎች ላይ ለሚፈጸም በደል እውነተኛው የእግዚአብሔር ፍርድ አጸፋዊ ምላሽ ነው። ሰዎች እንደሚያስቡት (1፥11) ያለፈ ነገር (ቊ15) ትርጒም አልባ አይደለም፤ ሰዎች የሚሰጡትን የተጣመመ ፍርድ (ቊ16) እግዚአብሔር ያያል (12፥14)።

3፥18 *እንደ እንስሳት፤* "ከፀሓይ በታች" ሰው እንስሳት እንደሚሞቱ ይሞታል፤ ነገር ግን ሰው ከእንስሳት ይልቅ ይህን እውነታ እንዲያስተውልና በደብዛዛ የዘላለማዊነት ዕውቀቱም (ቊ11) ሐዘን እንዲሰማው መደረግ አለበት።

ነው፤ አንዱ እንደሚሞት፣ ሌላውም እንዲሁ
ይሞታል። ሁሉ አንድ ዐይነት እስትንፋስ[m]
አላቸው፤ ሰውም ከእንስሳ ብልጫ የለውም፤
ሁሉም ከንቱ ነው። 20ሁሉም ወደ አንድ
ቦታ ይሄዳሉ፤ ሁሉም ከዐፈር እንደ ሆኑ፣
ተመልሰው ወደ ዐፈር ይሄዳሉ። 21የሰው
መንፈስ ወደ ላይ መውጣቱን፣ የእንስሳ እስት
ንፋስ[m] ደግሞ ወደ ታች ወደ ምድር መው
ረዱን ማን ያውቃል?"

22ስለዚህ ለሰው ዕጣ ፈንታው ስለ ሆነ፣
በሥራው ከመደሰት የተሻለ ነገር እንደ
ሌለው አየሁ፤ ከእርሱ በኋላ የሚሆነውንስ
ተመልሶ እንዲያይ የሚያደርገው ማን ነው?

## ግፍ፣ጥረት፣ብቸኝነት

4 እንደ ገና ከፀሓይ በታች የሚደረገውን
ግፍ ሁሉ አየሁ፤ አስተዋልሁም፤
የተገፉትን ሰዎች እንባ ተመለከትሁ፤
የሚያጽናናቸውም አልነበረም፤
ኀይል በሚገፏቸው ሰዎች እጅ ነበረ፤
የሚያጽናናቸውም አልነበረም።
2እኔም የቀድሞ ሙታን፣
ዛሬ በሕይወት ካሉት ሕያዋን ይልቅ፣
ደስተኞች እንደ ሆኑ ተናገርሁ።
3ነገር ግን ከሁለቱም ይልቅ፣
ገና ያልተወለደው፣
ከፀሓይ በታች የሚደረገውንም፣
ክፉት ያላየው ይሻላል።

4እንዲሁም ጥረትና የሥራ መከናወን ሁሉ
ሰው በባልንጀራው ላይ ካለው ቅናት እንደ
ሚመነጭ ተመለከትሁ፤ ይህም ደግሞ ከንቱ፣
ነፋስንም እንደ መከተል ነው።

5ሰነፍ እጁን አጣጥፎ ይቀመጣል፤
የገዛ ራሱንም ሥጋ ይበላል።
6በድካምና ነፋስን በመከተል
ከሚገኝ ሁለት ዕፍኝ ይልቅ፣
በርጋታ የሚገኝ አንድ ዕፍኝ ይሻላል።

7ደግሞም ከፀሓይ በታች ከንቱ የሆነን ነገር
አየሁ፤

8ልጅም ሆነ ወንድም የሌለው፣
ብቸኛ ሰው አለ፤
ጥረቱ ማለቂያ የለውም፤
ዐይኑም ባለው ሀብት ገና አልረካም፤
እርሱም፣ "ለማን ብዬ ነው የምደክመው?
ራሴን ከማስደሰትስ የምቈጠበው
ለምንድን ነው?" ብሎ ጠየቀ፤
ይህም ደግሞ ከንቱ፣
የጭንቅ ኑሮ ነው።

9ለሥራቸው መልካም ውጤት ስለሚያገኙ፣
ከአንድ፣ ሁለት መሆን ይሻላል፤
10አንዱ ቢወድቅ፣
ባልንጀራው ደግፎ ያነሣዋል።
ቢወድቅ የሚያነሣው ረዳት የሌለው ግን፣
እንዴት አሳዛኝ ነው!
11ደግሞም ሁለቱ አብረው ቢተኙ
ይሞቃቸዋል፤
ነገር ግን አንዱ ብቻውን እንዴት
ሊሞቀው ይችላል?
12አንድ ሰው ብቸኛውን ቢያጠቃውም፣
ሁለት ከሆኑ ይመክቱታል፤
በሦስት የተገመደ ገመድም ቶሎ
አይበጠስም።

## በልጦ መገኘት ከንቱ ነው

13ምክርን መቀበል ከማያውቅ ሞኝና ሽማ
ግሌ ንጉሥ ይልቅ ጠቢብ የሆነ ድኻ ወጣት
ይሻላል። 14ወጣቱ ከእስር ቤት ወደ ንጉሥ
ነት የመጣ ወይም በግዛቱ ውስጥ በድኽነት
የተወለደ ሊሆን ይችላል። 15ከፀሓይ በታች
የሚኖሩና የሚመላለሱ ሁሉ፣ ንጉሡን የሚ
ተካውን ወጣት ተከትለውት አየሁ። 16በፊቱ
የነበረው ሕዝብ ሁሉ ቍጥር ስፍር አልነበ
ረውም፤ ከእርሱ በኋላ የመጡት ግን በተ
ተኪው አልተደሰቱም። ይህም ደግሞ ከንቱ፣
ነፋስንም እንደ መከተል ነው።

3፥19 መክ2፥14
3፥20 ዘፍ2፥7፤ ኢዮ34፥15
3፥21 መክ12፥7
3፥22 ኢዮ31፥2፤ መክ2፥24
4፥1 መዝ12፥5፤ ሰቆ1፥16
4፥2 ኢዮ3፥17፤ 10፥18፤ኤር20፥17-18፤22፥10
4፥3 ኢዮ3፥16:22
4፥4 መክ1፥14
4፥5 ምሳ6፥10
4፥6 ምሳ15፥16-17፤ 16፥8
4፥8 ምሳ27፥20

[m]19 ወይም መንፈስ
[m]21 ወይም የሰው መንፈስ ወደ ላይ እንደሚሄድ ወይም የእን
ስሳት መንፈስ

3፥19 *አንድ ዐይነት እስትንፋስ፤* መዝ 104፥27-30 ይመ።

3፥20 *ወደ አንድ ቦታ፤* ወደ ገነት ወይም ወደ ሲኦል ሳይሆን፣ በግልጽ እንደሚታየው፣ እንስሳት ወደ ዐፈር እንደሚመለሱ ሁሉ፣ የሰውም ዕጣ ፈንታ ወደ ዐፈር መመለስ እንደ ሆነ ያመለክታል፤ ሕይወት ያላቸው ነገሮች ሁሉ በሞት እኩል ናቸውና (ዘፍ 3፥19፤ መዝ103፥14 ይመ)።

3፥21 *ማን ያውቃል?* 2፥19 እና ማብ ይመ፤ ከ12፥7 ጋር ያነጻጽሩ። ከመገመት በስተቀር ሰው በራሱ ትክክለኛውን ነገር ሊያውቅ አይችልም። ለጥያቄው የተሰጠው መልስ በመጀመሪያ ግልጽ አልነበረም (መዝ16፥9-11፤ 49፥15፤ 73፥23-26፤ ኢሳ 26፥19፤ ዳን12፥2-3)፤ በኋላ ግን በወንጌል አማካይነት ግልጽ ሆኖ አል (2ጢሞ1፥10)።

3፥22 *የተሻለ ነገር እንደሌለው፤* ሥራውም ቢሆን በራሱ የመጨረሻ ተደርጎ ከተወሰደ ትርጕም አይሰጥም (4፥4፤ 9፥9 ይመ)። ሥራን ከእግዚአብሔር የተሰጠ ጸጋ አድርገው ከተቀበሉት (ቍ 13) ግን ዋጋ አለው (ቍ 14)።

4፥1 *ግፍ፤* በ3፥16 ላይ የተጠቀሰ መሪ ሐሳብ ሲሆን፣ በሰው ሕይወት ውስጥ ከሚከሠቱ አሳዛኝ ነገሮች አንዱ ነው። ሕይወት ትርጕም ሲያጣ ያሳዝናል። በሕይወት አስከፊ ገጽታ ውስጥ ማለፍ ደግሞ እጅግ ይመራል።

4፥2 *ካሉት ሕያዋን ይልቅ ደስተኞች፤* ኢዮ3፤ ኤር 20፥14-18 ይመ። የበለጠውን ነገር ተስፋ ስለሚያደርግ እምነት ለማስተዋል ሮሜ 8፥35-39 ይመ።

*4፥4-6፤* ሥራ መሥራትም ሆነ አለመሥራት ደስታ አያስገኝም።

4፥4 *ጥረትና የሥራ መከናወን ሁሉ፤* እግዚአብሔር ካልባረከው፣ ይህም ቢሆን ከንቱ ነው (3፥13 ይመ፤ ዘፍ39 ላይ ካለው የዮሴፍ ታሪክ ጋር ያነጻጽሩ)።

*4፥5፤* በ10፥18፤ ምሳ 6፥6-11፤ 24፥30-34 ላይ የሰነፍ ሰው ውድቀት ምን እንደሚመስል በግልጽ ተጠቅሶአል።

4፥6 *በርጋታ፤* ምሳ 30፥7-9 ይመ። ጳውሎስ በዚህ ሐሳብ ላይ የመጨረሻውን ቃል ይናገራል (ፊል 4፥11-13)።

*4፥7-12፤* ክርስቲያን ያልሆነ ብቸኛ ሰውም ቢሆን፣ ሕይወቱ ትርጕም የለሽና አስቸጋሪ ይሆንበታል።

4፥12 *ሁለት … በሦስት፤* ከፍተኛ ጥንካሬን የሚያሳይ አገላለጽ ነው።

*4፥13-16፤* ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚደረግ ሩጫ የዓለማውያን ሕይወት ትርጕም የለሽነት ሌላው ምሳሌ ነው።

*5፥1-7፤* የዚህ ክፍል መሪ ሐሳብ ጥራዝ ነጠቅ ሃይማኖት ከንቱ መሆኑን የሚያመለክት ነው፤ ይህም በችኰላ ስእለት መሳል

### እግዚአብሔርን ፍራ

5 ወደ እግዚአብሔር ቤት ስትሄድ እግርህን
ጠብቅ። ለመስማት መቅረብ የሰነፎ
ችን መሥዋዕት ከማቅረብ ይበልጣል፤ እነ
ርሱ ክፉ እንደሚሠሩ አያውቁምና።

2በአፍህ አትፍጠን፤
በእግዚአብሔርም ፊት ማንኛውንም ነገር
ለመናገር፣
በልብህ አትቸኰል፤
እግዚአብሔር በሰማይ፣
አንተ ደግሞ በምድር ነህ፤
ስለዚህ ቃልህ ጥቂት ይሁን።
3በሥራ ብዛት ሕልም እንደሚታይ፣
ብዙ ቃል ባለበትም የሞኝ ንግግር
ይገለጣል።

4ለእግዚአብሔር ስእለትን በተሳልህ ጊዜ ለመ
ፈጸም አትዘግይ፤ በሰነፎች ደስ አይለው
ምና፤ ስእለትህን ፈጽም። 5ስእለት ተስሎ
ካለመፈጸም፣ አለመሳል ይሻላል። 6አንደበ
ትህ ወደ ኀጢአት እንዲመራህ አትፍቀድ፤
ለቤተ መቅደስ መልእክተኛም፣ "የተሳል
ሁት በስሕተት ነበር" አትበል። እግዚአብሔር
በተናገርኸው ተቈጥቶ የእጅህን ሥራ ለምን
ያጥፋ? 7ብዙ ሕልምና ብዙ ቃል ከንቱ
ነው፤ ስለዚህ እግዚአብሔርን ፍራ።

### ባለጠግነት ከንቱ ነው

8በአገር ውስጥ ድኻ ተጨቍኖ፣ ፍትሕ
ተጓድሎ፣ መብትም ተረግጦ ብታይ፣ እንደ
ነዚህ ባሉ ነገሮች አትደነቅ፤ ምክንያቱም
አንዱን አለቃ የበላዩ ይመለከተዋል፤ በእነዚህ
በሁለቱም ላይ ሌሎች ከፍ ያሉ አሉ። 9ከም
ድሩ የሚገኘው ትርፍ ለሁሉም ነው፤ ንጉ
ሡም ራሱ የሚጠቀመው ከዕርሻ ነው።

10ገንዘብን የሚወድ፣ ገንዘብ አይበቃውም፤
ብልጽግናም የሚወድ፣ በትርፉ አይረካም፤
ይህም ከንቱ ነው።

11ሀብት በበዛ ቍጥር፣
ተጠቃሚውም ይበዛል፤
በዐይኑ ብቻ ከማየት በቀር
ታዲያ፣ ለባለቤቱ ምን ይጠቅመዋል?

5፥2 መሳ11፥35፤ ኢዮ6፥24፤ ምሳ20፥25
5፥3 ኢዮ20፥8፤ መክ10፥14
5፥4 ዘኍ30፥2-4፤ ዘዳ23፥21፤መሳ 11፥35፤መዝ66፥13-14፤119፥60
5፥5 ዘኍ30፥24፤ ዮና2፥9
5፥7 መክ3፥14
5፥8 መዝ12፥5
5፥12 ኢዮ20፥20
5፥13 መክ6፥1-2
5፥15 ኢዮ1፥21፤ መዝ49፥17፤ መክ1፥3፤1ጢሞ6፥7
5፥16 መክ1፥3
5፥18 መክ2፥3:24
5፥19 1ዜና29፥12፤ ኢዮ31፥2፤ መክ2፥24፤6፥2
5፥20 ዘዳ12፥7:18
6፥2 መክ5፥13:19

12ጥቂትም ይሁን ብዙ ቢበላ፣
የሠራተኛ እንቅልፍ ጣፋጭ ነው፤
የሀብታም ሰው ብልጽግና ግን
እንቅልፍ ይነሣዋል።

13ከፀሓይ በታች የሚያሳዝን ክፉ ነገር አየሁ:-
ይህም ለባለቤቱ ጕዳት የተከማቸ ሀብት፣
14ወይም በአንድ መጥፎ አጋጣሚ የጠፋ
ብልጽግና ነው፤
ልጅ ሲወልድም፣
ለእርሱ የሚያስቀርለት ምንም ነገር
አይኖርም።
15ሰው ከእናቱ ማሕፀን
ዕራቍቱን ይወለዳል፤
እንደ መጣው እንዲሁ ይመለሳል።
ከለፋበትም ነገር፣
አንድም እንኳ በእጁ ይዞ ሊሄድ አይችልም።

16ይህ ደግሞ እጅግ ክፉ ነገር ነው፤

ሰው እንደ መጣ እንዲሁ ይሄዳል፤
የሚደክመው ለነፋስ ስለ ሆነ፣
ትርፉ ምንድ ነው?
17በብዙ ጭንቀት፣ መከራና ብስጭት፣
ዘመኑን ሁሉ በጨለማ ውስጥ ይበላል።

18የሰው ዕጣው ይህ ስለ ሆነ፣ እግዚአብሔር
በሰጠው በጥቂት ዘመኑ ከፀሓይ በታች
በሚደክምበት ነገር ርካታን ያገኝ ዘንድ፣
መብላቱና መጠጣቱም መልካምና ተገቢ
መሆኑን ተገነዘብሁ። 19እግዚአብሔር ለሰው
ባለጠግነትና ሀብት መስጠቱ፣ እንዲደሰትበ
ትም ማስቻሉ፣ ዕጣውን እንዲቀበልና በሥ
ራውም እንዲደሰት ማድረጉ፣ ይህ የእግዚ
አብሔር ስጦታ ነው። 20እግዚአብሔር የልብ
ደስታ ስለሚሰጠውም በሕይወቱ ዘመን
ያሉትን ቀናት እምብዛም አያስባቸውም።

6 ከፀሓይ በታች ሌላ ክፉ ነገር አየሁ፤
እርሱም ለሰዎች እጅግ የሚከብድ ነው፤
2ሰው ልቡ የሚሻውን እንዳያጣ፣ እግዚአብሔር
ባለጠግነትን፣ ሀብትንና ክብርን ይሰጠዋል፤
እግዚአብሔር ግን እንዲደሰትበት ሥልጣን አል
ሰጠውም፤ ይልቁን ባዕድ ይደሰትበታል።
ይህም ከንቱ፣ እጅግም ክፉ ነገር ነው።

በሚያስከትለው መዘዝ ተንጸባርቆአል።

5፥1 *እግርህን ጠብቅ፤* ምን ማለትና ምን ማድረግ እንደሚገባህ በጥንቃቄ አስብ ማለት ነው። *ለመስማት፤* መታዘዝን ያመለክታል። በ1ሳሙ 15፥22 ላይም ጸሓፊው የዚህን ቃል የዕብራይስጥ ግስ በመጠቀም እውነተኛውን አምልኮ እውነተኛ ካልሆነው አምልኮ ጋር ያነጻ ጽራል። *መሥዋዕት፤* ምናልባት በቍ 4-6 ላይ ከተጠቀሰው ስእለት ጋር የተያያዘ ይሆናል።

5፥2 *በአፍህ አትፍጠን፤* ፈጥኖ ስእለትን እንደ መሳል ያለውን ነገር ማድረግ ትክክል እንዳልሆነ ያሳያል።

*5፥3፤* ምሳሌያዊ አነጋገር ነው። የተራበ ሰው ድግስ ባጋጠመኝ ብሎ እንደሚያስብ፣ የተጨነቀም ሰው ታላቅ ደስታን ይመኛል፤ በምኞቱም ውስጥ ሆኖ ብዙ ቃል በመናገር በችኰላ ለእግዚአብሔር ስእለት ይሳላል (ቍ 7 ይመ)።

5፥4 *ስእለትን፤* ዘዳ 23፥21-23፤ 1ሳሙ1፥11:24-28 ይመ። *በሰነፎች ደስ አይለውምና፤* በመጽሐፍ ቅዱስ ሰነፍ መማር የማይችል ብቻ ሳይሆን፣ የማይፈልግም መሆኑ ተገልጾአል (ምሳ 1፥20-27፤ የዕብራይስጡ ቃል የሥነ ምግባር ጒድለት መሆኑን ያመለክታል)።

5፥6 *መልእክተኛም፤* ሚል 2፥7 ይመ።

5፥8 *አትደነቅ፤* ስለ ኀብረተ ሰብ የሚናገረውን ሌላ ክፍል ለማስተዋል 4፥1-3 ይመ። በሰው ልብ ያለውን እንደሚያቀው እንደ ኢየሱስ (ዮሐ 2፥25)፣ ይህ ሰባኪ የተሳሳተ ወይም ተምኔታዊ ሐሳብ አልነበረውም።

5፥9 *ንጉሡም ... የሚጠቀመው ከእርሻ ነው፤* የአሞ 7፥1 ማብ ይመ።

*5፥10፤* የሀብት ብዛት ርካታን አያስገኝም (1ጢሞ 6፥9-10 ይመ)።

*5፥11-12፤* ሀብት ሲበዛ ጭንቀትን ያስከትላል።

5፥13 *ጕዳት፤* የሀብት ብዛት ከሚያመጣው ሥጋት የተነሣ ማለት ነው።

5፥15 *አንድም እንኳ ... ይዞ፤* ሉቃ 12፥14-21 ይመ።

*5፥18-20፤* የ2፥24-25 ማብ ይመ።

6፥2-3፡6 *እንዲደሰትበት፤* በቍ 2 ላይ የተጠቀሰው ሐሳብ ከ5፥19 ጋር ሲነጻጸር፣ እግዚአብሔር በሰጠው በረከት በመጠቀም የሚገኘው ደስታ የእግዚአብሔር ነጻ ስጦታ እንጂ መብት እንዳልሆነ ያመለክታል። እግዚአብሔር ይህን እውነት የሚዘነጋውን

3አንድ ሰው መቶ ልጅ ሊኖረውና ብዙ
ዓመት ሊኖር ይችላል፤ ምንም ያህል ይኑር፣
በሀብቱ ደስ ካልተሰኘበትና በአግባብ ካልተቀ
በረ፣ ከእርሱ ይልቅ ጭንጋፍ ይሻላል እላ
ለሁ፤ 4ምክንያቱም በከንቱ ይመጣል፤ በጨ
ለማም ይሄዳል፤ ስሙም በጨለማ ተሸፍኖ
አል። 5ፀሓይን ባያይና ምንም ነገር ባያውቅ
እንኳ፣ እርሱ ከዚያ ሰው ይልቅ ዕረፍት
አለው፤ 6ሁለት ጊዜ ሺህ ዓመት ቢኖር
ነገር ግን በሀብቱ ደስ ባይሰኝበት ሁሉ
ወደዚያ ስፍራ የሚሄድ አይደለምን?

7የሰው ጥረት ሁሉ ለአፉ ነው፤
ፍላጎቱ ግን ፈጽሞ አይረካም።
8ጠቢብ ከሞኝ ይልቅ ምን ብልጫ አለው?
ድኻስ በሌሎች ፊት እንዴት እንደሚኖር
በማወቁ፣
ትርፉ ምንድን ነው?
9በምኞት ከመቅበዝበዝ፣
በዐይን ማየት ይሻላል፤
ይህም ደግሞ ከንቱ፣
ነፋስንም እንደ መከተል ነው።

10አሁን ያለው ሁሉ አስቀድሞ ስም
የተሰጠው ነው፤
ሰው የሚሆነውም አስቀድሞ የታወቀ
ነው፤
ከራሱ ይልቅ ከሚበረታ ጋር፣
ማንም አይታገልም።
11ቃል በበዛ ቍጥር፣
ከንቱነት ይበዛል፤
ይህ ታዲያ ለሰው ምን ይጠቅማል?

12ሰው በሕይወት ሳለ፣ እንደ ጥላ በሚያ
ልፉት ጥቂትና ከንቱ በሆኑት ቀኖቹ፣ ለሰው
መልካም የሆነውን የሚያውቅ ማን ነው?
እርሱ ከሄደ በኋላስ ከፀሓይ በታች የሚሆነ
ውን ማን ሊነግረው ይችላል?

## ጥበብ

7 መልካም ስም ከመልካም ሽቱ ይበልጣል፤
ከልደትም ቀን የሞት ቀን ይሻላል።
2ወደ ግብዣ ቤት ከመሄድ፣
ወደ ሐዘን ቤት መሄድ ይሻላል፤

6፥3 ኢዮ 3፥3፡6
6፥6 መክ2፥14
6፥7 ምሳ27፥20
6፥8 መክ2፥15
6፥9 መክ1፥14
6፥10 መክ3፥15
6፥12 1ዜና29፥15፤ ኢዮ10፥20፤14፥2፤ 20፥8፤መዝ39፥6
7፥1 ኢዮ10፥18፤ ምሳ22፥1፤ማሕ1፥3
7፥2 ምሳ11፥19፤ መክ2፥14
7፥3 ምሳ 14፥13
7፥4 መክ2፥1፤ ኤር16፥8
7፥5 ምሳ13፥18፤ 15፥31-32
7፥6 መዝ58፥9፤ ምሳ14፥13
7፥7 ዘፀ18፥21፤ 23፥8
7፥8 ምሳ14፥29
7፥9 ምሳ14፥29፤ ማቴ5፥22
7፥10 መዝ77፥5
7፥11 መክ2፥13፤ 11፥7
7፥13 መክ1፥5፤ 2፥24
7፥14 ኢዮ1፥21፤ መክ2፥24

ሞት የሰው ሁሉ ፍጻሜ ነውና፤
ሕያው የሆነም ይህን ልብ ማለት
ይገባዋል።
3ሐዘን ከሣቅ ይሻላል፤
ያዘነ ፊት ለልብ መልካም ነውና።
4የጠቢባን ልብ በሐዘን ቤት ነው፤
የሞኞች ልብ ግን በደስታ ቤት ነው።
5የሞኞችን መዝሙር ከመስማት፣
የጠቢባንን ሰዎች ተግሣጽ መስማት
ይሻላል።
6የሰነፎች ሣቅ፣
ከድስት ሥር እንደሚንጣጣ የእሾኽ ማገዶ
ነው፤
ይህም ደግሞ ከንቱ ነው።

7ግፍ ጠቢብን ሞኝ ያደርጋል፤
ጉቦም ልብን ያበላሻል።

8የአንድ ነገር ፍጻሜ ከጅማሬው ይሻላል፤
ትዕግሥተኛም ከትዕቢተኛ ይሻላል፤
9የሞኞች ቍጣ በዕቅፋቸው ውስጥ ስለ ሆነ፣
በመንፈስህ ለቍጣ አትቸኰል።

10አንተም፣ "ከእነዚህ ቀናት የቀድሞዎቹ ለምን
ተሻሉ?" አትበል፤
እንዲህ ያሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ
ጠቢብነት አይደለምና።

11ጥበብ እንደ ርስት መልካም ነገር ነው፤
ጠቃሚነቱም ፀሓይን ለሚያዩ ሰዎች
ነው።
12ገንዘብ ጥላ ከለላ እንደ ሆነ ሁሉ፣
ጥበብም ጥላ ከለላ ነው፤
የዕውቀት ብልጫዋ ግን፣
ጥበብ የባለቤቷን ሕይወት መጠበቋ
ነው።

13እግዚአብሔር ያደረገውን ተመልከት፤

እርሱ ያጣመመውን፣
ማን ሊያቃናው ይችላል?
14ጊዜው መልካም ሲሆን፣ ደስ ይበልህ፤
ጊዜው ክፉ ሲሆን ግን ይህን አስብ፤
እግዚአብሔር አንዱን እንዳደረገ፣
ሌላውንም አድርጎአል፤
ስለዚህ ሰው ስለ ወደ ፊት ሁኔታው፣

ሰው ሞኝ ይለዋል (ሉቃ 12፥20)።

6፥3 *በሚገባ ካልተቀበረ፤* እንደ ንጉሥ ኢዮአቄም (ኤር 22፥18-19) ሳይለቀስለትና ተገቢው ክብር ሳይሰጠው እንደ ሚቀበር ያመለክታል። *ጭንጋፍ፤* ለዓለማዊ ሰው፣ ሕይወት ወደ ሞት የሚወስድ ከንቱ ጒዞ ነው፤ አቋራጩና ቀላሉ መንገድ ሞቶ መወለድ ነው (ከኢዮ 3፥16፤ ከመዝ 58፥8 ጋር ያነጻጽሩ)።

6፥6 *ወደዚያ ስፍራ፤* እዚህም ላይ ከሞት በኋላ ስለሚሆ ነው ሳይሆን (ቍ12፤ 2-21 ይመ)፣ ሰው ሁሉ ሟች ስለ መሆኑ ይገልጻል።

*6፥7-12፤* ሰባኪው በራስ መርካትን በመቃወም የተለያዩ ሐሳ ቦችን ይጠቍማል፤ የሕይወት ጥቅም ጊዜያዊ (ቍ 7)፣ አወዛጋቢ (ቍ8) እና የማይጨበጥ መሆኑን (ቍ9)፣ የፈጠራ ችሎታችን፣ ኀይላችንና ጥበባችንም ውሱን መሆኑን (ቍ10-11)፣ እንዲሁም ከሰው የሚገኝ ጥቅምና ወደፊት ሊሆን ያለው ነገር አስተማማኝ አለመሆኑን (ቍ12) ይናገራል።

6፥10 *ስም የተሰጠው፤* አስቀድሞ በእግዚአብሔር የተወሰነ መሆኑን ያሳያል። *የታወቀ፤*አስቀድሞ በእግዚአብሔር መታወቁን ያመለክታል። *ከራሱ ይልቅ ከሚበረታ፤* እግዚአብሔርን የሚያመ ለክት ነው።

6፥12 *እንደ ጥላ፤* 1ዜና 29፥15 ይመ።

7፥1 *የሞት ቀን፤* ለክርስቲያን ከሚወለድበት ቀን ይልቅ የሚሞትበት ቀን ይሻለዋል፤ ከእግዚአብሔር ጋር ለዘላለም ለመ ኖር እጅግ የተሻለውን አዲስ ሕይወት የሚጀምርበት ዕለት ነውና (2ቆሮ 5፥1-10፤ ፊል 1፥21-23)። ከደስታ ጊዜ ይልቅ በችግር ጊዜ ብዙ ነገር ልንማር እንደምንችል ሰባኪው በቍ 2-6 ላይ ገልጾአል።

7፥7 *ጉቦም፤* ማቴ28፥11-15፤ ሉቃ22፥4-6 ይመ።

7፥9 *ቍጣ፤* ምሳ16፥32፤ 17፥14፤ 1ቆሮ13፥4-5 ይመ።

7፥12 *ሕይወት መጠበቋ፤* ለዚህ ሐረግ የተሰጠው የዕብራ ይስጥ አገላለጽ፣ "ሕይወት ይሰጣል" ወይም "ሕይወት ያድናል" ማለት ሊሆን ይችላል (ምሳ 3፥13-18፤ 13፥14 ይመ)።

7፥13 *ማን ሊያቃናው ይችላል?* የእግዚአብሔርን ማንነት ያሳስባል፤ እግዚአብሔር የወሰነውን ነገር ሰው ሊለውጠው አይች ልም (የ1፥15 ማብ ይመ)።

7፥14 *እግዚአብሔር አንዱን እንዳደረገ፣ ሌላውንም አድ ርጎአታል፤* ከሮሜ 8፥28-29 ጋር ያነጻጽሩ።

ምንም ሊያውቅ አይችልም።
[15]በዚህ ከንቱ በሆነው ሕይወቴ እነዚህን ሁለቱን ነገሮች አይቻለሁ፤
ጻድቅ በጽድቁ ሲጠፋ፣
ኀጥእም በክፋቱ ዕድሜው ሲረዝም።
[16]እጅግ ጻድቅ፣
እጅግም ጠቢብ አትሁን፤
ራስህን ለምን ታጠፋለህ?
[17]እጅግ ክፉ አትሁን፤
ሞኝም አትሁን፤
ለምንስ ያለ ቀንህ ትሞታለህ?
[18]አንዱን ይዞ ሌላውንም አለመልቀቅ
መልካም ነው፤
እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው
ጽንፈኝነትን ያስወግዳል[ሀ]።
[19]በአንድ ከተማ ካሉ ዐሥር ገዦች ይልቅ፣
ጥበብ ጠቢቡን ሰው ኀያል
ታደርገዋለች።
[20]ትክክለኛውን ነገር የሚያደርግና ፈጽሞ
ኀጢአት የማይሠራ፣
ጻድቅ ሰው በምድር ላይ የለም።
[21]የሚነገረውን ቃል ሁሉ ለማዳመጥ አትሞክር፤
አለበለዚያ አገልጋይህ ሲረግምህ ትሰማ
ይሆናል፤
[22]ብዙ ጊዜ አንተ ራስህ፣
ሌሎችን እንደረገምህ ልብህ ያውቃልና
[23]እኔም ይህን ሁሉ በጥበብ ፈትኼ፣
"ጠቢብ ለመሆን ቈርጫለሁ" አልሁ፤
ይህ ግን ከእኔ የራቀ ነበር።
[24]ጥበብ ምንም ይሁን ምን፣
እጅግ ጥልቅና ሩቅ ነው፤
ማንስ ሊደርስበት ይችላል?
[25]ስለዚህ ጥበብንና የነገሮችን አሠራር
ለመመርመርና ለማጥናት፣
የክፋትን መጥፎነት፣
የሞኝነትንም እብደት ለማስተዋል፣
አእምሮዬን መለስሁ።
[26]ልቧ ወጥመድ፣
እጆቿም እግር ብረት የሆኑ፣
አሽክላ የሆነች፣
ከሞት የከፋችዋን ሴት አገኘሁ፤
እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ከእጇ ያመልጣል፤
ኀጢአተኛውን ግን አጥምዳ ትይዘዋለች።
[27]ሰባኪው[ለ] እንዲህ ይላል፤ "እነሆ፤ መርምሬ ያገኘሁት ነገር ይህ ነው፤
"የነገሮችን ብልኀት መርምሮ ለማግኘት፣
አንዱን በአንዱ ላይ በመጨመር፣
[28]ገና በመመርመር ላይ ሳለሁ፣
ግን ያላገኘሁት፣
ከሺህ ወንዶች መካከል አንድ ቅን ሰው
አገኘሁ፣
በእነዚያ ሁሉ መካከል ግን አንዲት ቅን
ሴት አላገኘሁም።
[29]ይህን አንድ ነገር ብቻ አገኘሁ፤
እግዚአብሔር ሰውን ቅን አድርጎ
መሥራቱን፣
ሰዎች ግን ውስብስብ ዘዴ ቀየሱ።"

8 ነገሮችን መግለጽ የሚችል፣
እንደ ጠቢብ ያለ ሰው ማን ነው?
ጥበብ የሰውን ፊት ታበራለች፤
የከበደ ገጽታውንም ትለውጣለች።

### ንጉሥን ታዘዝ

[2]በእግዚአብሔር ፊት መሐላ ስለ ፈጸምህ፣
የንጉሥን ትእዛዝ አክብር እልሃለሁ።
[3]ከንጉሥ ፊት ተጣድፈህ አትውጣ፤ የወደደ
ውንም ማድረግ ስለሚችል ለጥፋት አትሰ
ለፍ። [4]የንጉሥ ቃል በላይ ስለ ሆነ እርሱን፣
"ምን ታደርጋለህ?" ማን ሊለው ይችላል?
[5]እርሱን የሚታዘዝ ሁሉ አይጐዳም፤
ጥበበኛም ልብ ትክክለኛውን ጊዜና
ተገቢውን አሠራር ያውቃል።
[6]የሰው መከራ እጅግ ቢጫነውም፣
ለሁሉም ነገር ትክክለኛ ጊዜና ተገቢ
አሠራር አለው።
[7]ሰው የወደፊቱን ስለማያውቅ፣
ሊመጣ ያለውን ማን ሊነግረው ይችላል?
[8]ሰው ነፋስን መቈጣጠር አይችልም[ሐ]፤
በዕለተ ሞቱም ላይ ሥልጣን ያለው ማንም
የለም፤
በጦርነት ጊዜ ማንም ከግዴታ ነጻ

7፥15 ኢዮ7፥7፤ 21፥7፤መክ8፥12-14፤ኤር12፥1
7፥17 ኢዮ15፥32
7፥18 መክ 3፥14
7፥19 ምሳ8፥14፤ መክ2፥13
7፥20 2ዜና6፥36፤ ኢዮ4፥17፤መዝ14፥3፤ ምሳ20፥9፤ሮሜ3፥12
7፥21 ምሳ30፥10
7፥23 መክ1፥17
7፥24 ኢዮ28፥12
7፥25 ኢዮ28፥3፤ መክ1፥17
7፥26 ዘፀ10፥7፤መሳ 14፥15፤ምሳ2፥16-19፤ 5፥3-5፤7፥23፤22፥14
7፥27 መክ1፥1
7፥28 1ነገ11፥3
8፥3 መክ10፥4
8፥4 አስ1፥19
8፥6 መክ3፥1

[ሀ]18 ወይም *ሁለቱንም ይከተላቸዋል*
[ለ]27 ወይም *የጉባኤ መሪ*
[ሐ]8 ወይም *መንፈሱን ለማቈየት አይችልም*

7፥15 *ጻድቅ ... ሲጠፋ፤* ጽድቅ፣ ከመከራ ወይም ያለ ወቅቱ ከመሞት ላይከላከልልን ይችላል።
7፥16 *እጅግ ጻድቅ፣ ... እጅግም ጠቢብ አትሁን፤* እውነተኛው ጽድቅና ጥበብ ከጥፋት የማያድን ከሆነ፣ የሥርዐት ጽድቅና ጥበብ ለማንም እንደማይጠቅም ግልጽ ነው።
7፥17 *እጅግ ክፉ አትሁን፤* ከመጠን ያለፈ ክፋት አጕል ድፍረት ነው፤ ጥፋትንም ያስከትላል።
7፥18 *አንዱን ... ሌላውንም፤* እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው በጽድቅና በጥበብ የሚመራ ወግ አጥባቂነትንና ሥርዐተ አልበኛነትን በማስወገድ ሚዛናዊ ሕይወት ይኖረዋል።
7፥20 *ጻድቅ ሰው በምድር ላይ የለም፤* ዐቢይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ነው (ሮሜ3፥10-20)።
*7፥24፤* ኢዮ 28፥12-28፤ 1ቆሮ 2፥9-16 ይመ።
*7፥26፤* ምሳ 7፥6-27 ይመ።
7፥27 *ሰባኪው፤* የ1፥1 ማብ ይመ። *የነገሮችን ብልኀት መርምሮ ለማግኘት አንዱን በአንዱ ላይ በመጨመር፤* እንደ ዚህ ዐይነቱ አካሄድ መቆሚያ የለውም፤ የምናየውን ሁሉ አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ ልንተረጕምም አንችልም (3፥11)፤ የሰው ጥበብና መረዳት፣ ለተገለጠው እውነት ሁልጊዜ የሚገዛ መሆን አለበት።
7፥29 *እግዚአብሔር ሰውን ቅን አድርጎ መሥራቱን ... ግን፤* ዘፍ 3፥1-6፤ ሮሜ 5፥12 ይመ።
8፥2 *መሐላ ስለ ፈጸምህ፤* ለንጉሥ ታማኝ ሆኖ ለመገኘት ነው (1ዜና 29፥24 ይመ)። *የንጉሥን ትእዛዝ፤* መመሪያ ማውጣት (ቍ2) እና መመሪያውን በጥንቃቄ ማክበር (ቍ3-6) ለነጻነታችን ወሳኞች ናቸው።
8፥4 *"ምን ታደርጋለህ?" ማን ሊለው ይችላል?* ከኢሳ 45፥9፤ ከሮሜ 9፥20 ጋር ያነጻጽሩ።
8፥6 *የሰው መከራ፤* ሰው ከመከራው ይልቅ የንጉሡን ትእዛዝ አክብሮ ማየት አለበት።
8፥7-8 *ሰው ... ስለማያውቅ፣... ነፋስን መቈጣጠር አይችልም፤* መዝ3፥15፤ 2ቆሮ5፥1-10፤ ያዕ 4፥13-16 ይመ።

እንደማይሆን፣
ክፋትም የሚለማመዷትን አትለቃቸውም።

9ከፀሓይ በታች የተሠራውን ሁሉ በአእ
ምሮዬ መርምሬ፣ ይህን ሁሉ አየሁ። ሰው
ሰውን ለመጕዳት ገዥ የሚሆንበት ጊዜ
አለ። 10እንዲሁም ወደ ቅዱሱ ስፍራ ይመ
ጡና ይሄዱ የነበሩት ክፉዎች ተቀብረው
አየሁ፤ ይህን ባደረጉበት ከተማም ይመሰገኑ
ነበር[†]፤ ይህም ደግሞ ከንቱ ነው።
11በወንጀል ላይ ባፋጣኝ ፍርድ ካልተሰጠ፣
የሰዎች ልብ ክፉን በማድረግ ዕቅድ ይሞ
ላል። 12ኀጥእ መቶ ወንጀል ሠርቶ ዕድ
ሜው ቢረዝምም፣ እግዚአብሔርን የሚያከብሩ፣
ፈሪሀ እግዚአብሔር ያላቸው ሰዎች መልካም እን
ደሚሆንላቸው ዐውቃለሁ። 13ነገር ግን ክፉ
ዎች እግዚአብሔርን ስለማይፈሩ መልካም አይሆ
ንላቸውም፤ ዕድሜያቸው እንደ ጥላ አይረ
ዝምም።
14በምድር ላይ የሚከሠት ሌላም ከንቱ ነገር
አለ፤ ጻድቃን ለክፉዎች የሚገባውን፣ ክፉ ሰዎ
ችም ለጻድቃን የሚገባውን ይቀበላሉ፤ ይህም
ደግሞ ከንቱ ነገር ነው አልሁ። 15ለሰው፣ ከፀ
ሓይ በታች ከመብላት፣ ከመጠጣትና ከመደ
ሰት ሌላ የተሻለ ነገር ስለ ሌለ፣ በሕይወት ደስ
መሰኘት መልካም ነው አልሁ፤ ስለዚህ እግዚ
አብሔር ከፀሓይ በታች በሰጠው የሕይወት ዘመኑ
ሁሉ በሥራው ደስታ ይኖረዋል።
16ጥበብን ለማወቅና ሌት ተቀን እንቅልፍ
የማያውቀውን በምድር ያለውን የሰውን ድካም
ለመገንዘብ በአእምሮዬ ስመረምር፣ 17እግዚ
አብሔር ያደረገውን ሁሉ አየሁ። ከፀሓይ
በታች የሚደረገውን ማንም ሊያውቅ አይ
ችልም፤ ሰው ለመመርመር ብዙ ቢጥርም፣
ትርጕሙን ማግኘት አይችልም፤ ጠቢብም
እንኳ ዐውቀዋለሁ ቢል፣ ፈጽሞ ሊገነዘበው
አይችልም።

## የሁሉም የመጨረሻ ዕጣ ፈንታ

9 ስለዚህ ይህን ሁሉ በልቤ አስቤ እንዲህ
አልሁ፤ ጻድቃንና ጠቢባን፣ የሚሠሩትም
ሥራ በእግዚአብሔር እጅ ነው፤ ነገር ግን
ፍቅር ይሁን ወይም ጥላቻ የሚጠብቀውን
ማንም አያውቅም። 2ጻድቃንና ኀጥአን፣ ደጎ
ችና ክፉዎች[°]፣ ንጹሓንና ርኩሳን፣ መሥ
ዋዕት የሚያቀርቡና የማያቀርቡ የሁሉም
የመጨረሻ ዕጣ ፈንታ አንድ ነው።
ለደጉ ሰው እንደ ሆነው ሁሉ፣
ለኀጢአተኛውም እንዲሁ ነው፤
ለሚምሉት እንደ ሆነው ሁሉ፣
መሐላን ለሚፈሩትም እንዲሁ ነው።

3ከፀሓይ በታች በሁሉም ላይ የሚሆነው
ክፋት ይህ ነው፤ የሁሉም የመጨረሻ ዕጣ
ፈንታ አንድ ነው። በዚህም ላይ የሰዎች ልብ
በክፋት የተሞላ ነው፤ በሕይወት እያሉም
በልባቸው ውስጥ እብደት አለ፤ በመጨረሻም
ወደ ሙታን ይወርዳሉ። 4በሕያዋን መካከል
ያለ ማንኛውም ሰው ተስፋ አለው[†]፤ በሕ
ይወት ያለ ውሻ ከሞተ አንበሳ ይሻላልና!

5ሕያዋን እንደሚሞቱ ያውቃሉና፤
ሙታን ግን ምንም አያውቁምና፤
መታሰቢያቸው ይረሳል፤
ምንም ዋጋ የላቸውም።
6ፍቅራቸው፣ ጥላቻቸው፣
ቅናታቸውም ከጠፋ ቈይቶአል፤
ከፀሓይ በታች በሚሆነው ነገር ሁሉ፣
ፈጽሞ ዕጣ ፈንታ አይኖራቸውም።

7ሂድ፤ ምግብህን በደስታ ብላ፤ ወይንህንም
ልብህ ደስ ብሎት ጠጣ፤ ባደረግኸው ነገር
እግዚአብሔር ደስ ብሎታልና። 8ዘወትር ልብስህ
ነጭ ይሁን፤ ራስህንም ዘወትር በዘይት ቅባ።
9እግዚአብሔር ከፀሓይ በታች በሰጠህ በዚህ
ትርጕም የለሽ የሕይወት ዘመን ሁሉ፣
ከንቱ በሆኑትም ቀኖችህ ሁሉ ከምትወዳት
ሚስትህ ጋር ደስ ይበልህ፤ በሕይወትህና
ከፀሓይ በታች በምትደክምበት ነገር ሁሉ
ይህ ዕድል ፈንታህ ነውና። 10እጅህ የሚያ
ገኘውን ሥራ ሁሉ በሙሉ ኀይልህ ሥራው፤
ልትሄድበት ባለው መቃብር[‡] ውስጥ መሥ
ራትም ሆነ ማቀድ፣ ዕውቀትም ሆነ ጥበብ
የለምና።

8፥10 መክ1፥11
8፥12 ዘፀ1፥20፤ ዘዳ12፥28፤መክ3፥14
8፥13 ዘዳ4፥40፤ ኢዮ5፥26፤መዝ 34፥12፤መክ3፥14፤ ኢሳ65፥20
ኢዮ21፥7፤መክ7፥15
8፥15 ዘፀ32፥6፤መዝ 42፥8፤መክ2፥1:3
8፥16 መክ1፥13:17
8፥17 ኢዮ28፥3 :23፤ሮሜ11፥33
9፥1 መክ10፥14
9፥2 ኢዮ9፥22፤ መክ2፥14
9፥3 ኢዮ9፥22፤ 21፥26፤መክ2፥14፤ ኤር11፥8፤13፥10፤ 16፥12፤17፥9
9፥5 ኢዮ14፥21፤ መዝ9፥6፤መክ1፥11
9፥6 ኢዮ21፥21
9፥7 ዘኍ6፥20፥ መክ2፥24
9፥8 ራእ 3፥4
9፥9 ኢዮ31፥2፤ ምሳ5፥18
9፥10 ዘኍ16፥33፤ 1ሳሙ10፥7፤መዝ 6፥5፤መክ2፥24፤11፥6 ፤ኢሳ38፥18

†10 አንዳንድ የዕብራይስጥ ቅጆችና ሰብዓ ሊቃናት (አቍዊላ) እን
ዲሁ ሲሆኑ አብዛኞዎቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን ተረስተዋል
ይላሉ።
°2 ሰብዓ ሊቃናት (አቍዊላ) ቨልጌትና ሱርስት እንዲሁ ሲሆኑ
ዕብራይስጡ ግን ክፉዎች የሚለው የለም
†4 ወይም ታዲያ የሚመረጠው ምንድነው? ለሕያዋን ሁሉ
ተስፋ አለ
‡10 በዕብራይስጥ ሲኦል ማለት ነው

8፥10 *ክፉዎች ተቀብረው፤* ይህ ዐውደ ምንባብ ለክፉዎች ስለማይገባ ክብር ይናገራል (የ6፥3 ማብ ይመ፤ ከኢዮ 21፥28-33፤ ከሉቃ 16፥22 ጋር ያነጻጽሩ)።

*8፥11፤* የዘገየ ቅጣት የበለጠ ስህተት እንዲፈጸም ይገፋፋል።

8፥12 *ዐውቃለሁ፤* እዚህ ላይ ሰባኪው ገና በመመርመር ላይ እንዳለ ግን እንዳላገኘ ሰው ሳይሆን (7፥28) ከጽኑ እምነት የተነሣ ይናገራል። ለተመሳሳይ አገላለጽ 3፥17፤11፥9፤12፥14 ይመ።

*8፥14፤* ኢዮ 21-24 ላይ ይህን ሐሳብ በስፋት ያብራራል፤ መዝ 73 ሐሳቡ የሚያስከትለውን ከፍተኛ ስሜት ያሳያል፤ ዮሐ 5፥28-29 ደግሞ የመጨረሻውን ማብራሪያ ይሰጣል።

8፥15 *ከመብላትና ከመጠጣትና ከመደሰት፤* ከጊዜያዊ ምቾት አንጻር የተነገረ ነው (5፥19፤9፥7፤ ዘዳ 8 ይመ)። ይህ እንዲሁም በሉቃ 12፥19-20፤ 1ቆሮ 15፥32 ይመ።

8፥17 *ማንም ሊያውቅ አይችልም፤* እንድናውቅ የተፈቀደልንና ያልተፈቀደልን ነገር በዘዳ29፥29 ላይ ተመልክቶአል።

9፥1 *ፍቅር ይሁን ወይም ጥላቻ፤* ወደ ፊት የሚሆነው ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር እጅ ነው። የወደፊቱ መልካም ይሁን ወይም አይሁን የሚያውቅ ሰው የለም።

9፥2 *የመጨረሻ ዕጣ ፈንታ አንድ ነው፤* ጠቢቡና ሞኙ ብቻ ሳይሆኑ (2፥14)፣ ደጉና ክፉውም ሰው መጨረሻቸው አንድ እንደ ሆነ በ3፥20 ላይ ተመልክቶአል። በመጨረሻ እግዚአብሔር ለተደረገው ነገር ተገቢ ፍርድ እንደሚሰጥ ሰባኪው እርግጠኛ ለመሆኑ የ8፥12 ማብ ይመ።

9፥3 *ክፋት ... በክፋት፤* የጻድቁና የኀጥኡ በሞት አንድ መሆን አንዳንድ ሰዎችን ኀጢአት እንዲሠሩ ያደፋፍራቸዋል።

9፥5 *ምንም ዋጋ የላቸውም፤* የሞቱ ሰዎች በምድራዊ ሕይወት ለመደሰትና በድካማቸው ፍሬ ለመጠቀም ዕድል የላቸውም።

*9፥7፤* የ8፥15 ማብ ይመ።

*9፥10፤* ከቈላ 3፥23 ጋር ያነጻጽሩ።

11 ሌላም ነገር ከፀሐይ በታች አየሁ:-
ሩጫ ለፈጣኖች፣
ውጊያም ለኀያላን አይደለም፤
እንጀራ ለጥበበኞች፣
ወይም ባለጠግነት ለብልኆች፣
ወይም ሞገስ ለዐዋቂዎች አይሆንም፤
ጊዜና ዕድል ግን ሁሉን ይገናኛቸዋል::
12 ደግሞም የራሱን ጊዜ የሚያውቅ ሰው የለም፤
ዓሦች በክፉ መረብ እንደሚያዙ፣
ወይም ወፎች በወጥመድ
እንደሚጠመዱ፣
ሰዎችም ሳያስቡት በሚመጣባቸው፣
በክፉ ጊዜ ይጠመዳሉ::

### ጥበብ ከሞኝነት ይበልጣል

13 እንዲሁም እጅግ ያስገረመኝን ይህን
የጥበብ ምሳሌ ከፀሓይ በታች አየሁ:-
14 ጥቂት ሰዎች የሚኖሩባት አንዲት ትንሽ
ከተማ ነበረች፤ አንድ ኀያል ንጉሥም መጣ
ባት፤ ከበባት፤ በላይዋም ትልቅ ምሽግ ሠራ
ባት:: 15 በዚያችም ከተማ ጥበበኛ የሆነ አንድ
ድኻ ሰው ይኖር ነበር፤ በጥበቡም ከተማዋን
አዳናት፤ ነገር ግን ያን ድኻ ማንም አላስታ
ወሰውም:: 16 ስለዚህ፣ "ጥበብ ከኀይል ይበል
ጣል" አልሁ፤ ሆኖም የድኻው ጥበብ ተንቆ
አል፤ ቃሉም አልተሰማም::

17 ሞኞችን ከሚያስተዳድር ገዥ ጩኸት
ይልቅ፣
ጠቢብ በዝግታ የሚናገረው ቃል
ይደመጣል::
18 ጥበብ ከጦር መሣሪያ ይበልጣል፤
ነገር ግን አንድ ኀጢአተኛ ብዙ መልካም
ነገርን ያጠፋል::

# 10

የሞቱ ዝንቦች ሽቶን
እንደሚያገሙ፣
ትንሽ ሞኝነትም ጥበብንና ክብርን
ያቀላል::
2 የጠቢብ ልብ ወደ ቀኝ፣
የሞኝ ልብ ግን ወደ ግራ ያዘነብላል::
3 ሞኝ በጐዳና ሲሄድ ማስተዋል ይጐድለዋል፤
ጅል መሆኑንም ለማንም ይገልጻል::
4 የገዥ ቍጣ በተነሣብህ ጊዜ፣
ስፍራህን አትልቀቅ፤
ትዕግሥት ታላቁን ጥፋት ጸጥ ያደርጋልና::
5 ከፀሓይ በታች ያየሁት ክፉ ነገር አለ፤
ይህም ከገዥ የሚወጣ ስሕተት ነው፤
6 ሞኞች በብዙ የክብር ስፍራዎች ሲቀመጡ፣
ሀብታሞች ግን በዝቅተኛ ስፍራ ሆነዋል::
7 መሳፍንት እንደ ባሮች በእግራቸው ሲሄዱ፣
ባሮች ፈረስ ላይ ተቀምጠው አይቻለሁ::
8 ጕድጓድን የሚምስ ራሱ ይገባበታል፤
ቅጥርንም የሚያፈርስ እባብ ይነድፈዋል::
9 ድንጋይ የሚፈነቅል ይጐዳበታል፤
ግንድንም የሚፈልጥ አደጋ ላይ መውደቁ
አይቀርም::
10 መጥረቢያ ቢደንዝ፣
ጫፉም ባይሳል፣
በዙ ጕልበት ይጨርሳል፤
ብልኀት ግን ለውጤት ያበቃል::
11 እባብ በድግምት ከመፍዘዙ በፊት ቢነድፍ፣
ለደጋሚው ምንም አይጠቅመውም::
12 ከጠቢብ አፍ የሚወጣ ቃል ባለ ሞገስ ነው፤
ሞኝ ግን በገዛ ከንፈሩ ይጠፋል፤
13 ቃሉ በመጀመሪያ ሞኝነት ነው፤
በመጨረሻም ደግሞ ክፉ እብደት ነው፤
14 ሞኙም ቃልን ያበዛል::
የሚመጣውን የሚያውቅ የለም፤
ከእርሱ በኋላ የሚሆነውንስ ማን ሊነግረው
ይችላል?
15 የሞኝ ሥራ ራሱን ያደክመዋል፤
ወደ ከተማ የሚወስደውንም መንገድ
አያውቅም::
16 አንቺ፣ ንጉሥሽ ልጅ[1] የሆነ፣
መሳፍንትሽም በጠዋት ግብዣ የሚያደርጉ
ምድር ሆይ፤ ወዮልሽ!
17 አንቺ ንጉሥሽ ከተከበረው ዘር የሆነ፣
ለመስከር ሳይሆን ለብርታት፣
በተገቢው ጊዜ የሚበሉ መሳፍንት ያሉሽ
ምድር ሆይ፤ የተባረክሽ ነሽ፤
18 ሰው ሰነፍ ከሆነ ጣራው ይዘብጣል፤
እጆቹም ካልሠሩ ቤቱ ያፈሳል::

9፥11 ዘዳ8፥18፤ኢዮ 32፥13፤መክ2፥14፤ ኢሳ47፥10፤ኤር 9፥23፤አሞ2፥14-15
9፥12 መዝ73፥22፤ መሳ29፥6፤መክ2፥14
9፥13 2ሳሙ20፥22
9፥15 ዘፍ40፥14፤ መክ1፥11
9፥16 አስ6፥3
9፥18 መክ2፥13
10፥1 ምሳ13፥16፤ 18፥2
10፥3 ምሳ13፥16
10፥4 መክ8፥3፤ ምሳ16፥14
10፥6 ምሳ29፥2
10፥7 ምሳ19፥10
10፥8 አስ2፥23፤ መዝ9፥16፤57፥6፤አሞ 5፥19
10፥9 ምሳ26፥27
10፥11 መዝ58፥5፤ ኢሳ3፥3
10፥12 ምሳ10፥6፡ 32፤14፥3፤15፥2፤18፥7
10፥14 መክ5፥3፤ 9፥1
10፥16 ኢሳ3፥4-5 :12
10፥17 ዘዳ14፥26፤ 1ሳሙ25፥36፤ ምሳ31፥4
10፥18 ምሳ20፥4፤ 24፥30-34

[1]16 ወይም አሽከር

9፥11 *ጊዜና ዕድል፤* ማን እንደሚሳካለት እርግጠኛ መሆን አይቻልም፤ ይህም ሁነቶች ሁሉ በሰው ቍጥጥር ሥር አለመሆና ቸውን ያረጋግጣል::

9፥12 *ጊዜ፤* የመከራና የጥፋት ጊዜ ነው:: *ሰዎችም ... ይጠመዳሉ፤* ማንም ሰው መቼ እንደሚያሸንፍ ወይም መቼ እንደሚሸነፍ ማወቅ ስለማይችል፣ አስቀድሞ ድል አደርጋለሁ ብሎ መናገር አስቸጋሪ ነው::

9፥15 *ነገር ግን ... ማንም አላስታወሰውም፤* ሰው በራሱ ጥበብ ከመጠን በላይ እንዳይመካ የተሰጠ ተጨማሪ ማስጠንቀቂያ ነው:: የሰው ጥበብ ታላቅነት ይደበዝዛል፣ መልካምነቱም ይበላሻል (ቍ 18) ለሞትም መፍትሔ የለውም (2፥15-16)::

10፥1 *ትንሽ ሞኝነትም ... ያቀላል፤* በ2ነገ 20፥12-19 ላይ የተገለጸው ታሪክ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው::

10፥2 *ወደ ቀኝ ... ወደ ግራ፤* ብዙ ወይም ጥቂት በጎነ ትን የሚያመለክት ነው (ከዘፍ48፥13-20 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ወይም በአይሁድ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ እንደ ተጠቀሰው፣ ጥሩና መጥፎ የሆነውን ነገር የሚያመለክት ነው::

10፥5 *ከገዥ ... ስሕተት፤* ሰባኪው በሰው አስተዳደር ውስጥ የተመለከተውን ነገር ለማስተዋል ቍ 4:6-7:16-17:20፤ 3፥16፤ 4፥1-3:13-16፤ 5፥8-9፤ 8፥2-6: 10፣11፤9፥17 ይመ::

10፥12 *ቃል፤* በቅኔ መጻሕፍት ውስጥ ተደጋግሞ ተጠቅ ሶአል (ምሳ 15 ይመ) ::

10፥15 *ወደ ከተማ የሚወስደውንም መንገድ አያውቅም፤* በመጽሐፍ ቅዱስ ሞኝ የሚባለው የእግዚአብሔርን ቃል ለመማር የማይፈልግ ሰው ሲሆን (የ5፥4 ማብ ይመ)፣ እዚህ ላይ የተጠ ቀሰው ምሳሌያዊ አባባል ግን ከዚህ የከፋ ትርጕም ያለውን ያመ ለክታል::

10፥16 *ንጉሥሽ ልጅ የሆነ፤* በ4፥13 ላይ እንደ ተጠቀ ሰው "ጠቢብ የሆነ ድኻ ወጣት" ሳይሆን፣ ያለ ድካም የከበረው ንና ደካማ አስተሳሰብ ያለውን አምባገነን ንጉሥ ያሳያል፤ ያለ አግባብ ሥልጣን ላይ በመውጣት ለአጭጭር ጊዜ እስራኤልን ስለ ገዙትና ለውድቀት ስለዳረጉት አረማውያን ነገሥታት በ2ነገ 15፥8-15፤ በሆሴ 7፥3-7 ይመ::

10፥18 *ሰነፍ ... እጆቹም ካልሠሩ፤* የ4፥5 ማብ ይመ::

19 ግብዣ ለሣቅ ያዘጋጃል፤
ወይንም ሕይወትን ያስደስታል፤
ገንዘብም ካለ ሁሉ ነገር አለ።

20 በሐሳብህም እንኳ ንጉሥን አትንቀፍ፤
በመኝታ ክፍልህም ባለጠጋን
አትርገም፤
የሰማይ ወፍ ቃልህን ልትወስድ፣
የምትበረዋም ወፍ የምትለውን
ልታደርስ ትችላለችና።

### እንጀራ በውሃ ላይ

**11** እንጀራህን በውሃ ላይ ጣል፤
ከብዙ ቀን በኋላ መልሰህ
ታገኘዋለህና።
2 ሀብትህን ሰባት ቦታ፣ እንዲያውም ስምንት
ቦታ ከፍለህ አስቀምጥ፤
በምድሪቱ ላይ የሚመጣውን ጥፋት
አታውቅምና።

3 ደመናት ውሃ ካዘሉ፣
በምድር ላይ ዝናብን ያዘንባሉ፤
ዛፍ ወደ ደቡብም ሆነ ወደ ሰሜን ቢወድቅ፣
በወደቀበት ቦታ በዚያ ይጋደማል።
4 ነፋስን የሚጠባበቅ አይዘራም፤
ደመናትንም የሚያይ አያጭድም።

5 የነፋስን መንገድ እንደማታውቅ፣
ሕይወት ወይም መንፈስ በእናት ማሕፀን
ውስጥ ወደሚገኘው አካል እንዴት
እንደሚገባም[1] እንደማታውቅ ሁሉ፣
ሁሉን ሠሪ የሆነውን፣ የእግዚአብሔርን ሥራ
ማስተዋል አትችልም።

6 ጠዋት ላይ ዘርህን ዝራ፤
ማታም ላይ እጅህ ሥራ አይፍታ፤
ይህ ወይም ያ፣
ወይም ሁለቱ መልካም ይሁኑ፣
የቱ እንደሚያፈራ አታውቅምና።

### ወጣት ሳለህ ፈጣሪህን አስብ

7 ብርሃን መልካም ነው፤
ፀሐይንም ማየት ለዐይን ደስ ያሰኛል።

8 ሰው ምንም ያህል ብዙ ዓመት ቢኖር፣
በእነዚህ ሁሉ ይደሰት፤
ነገር ግን ጨለማዎቹንም ቀናት ያስብ፤
እነርሱ ይበዛሉና፤
የሚመጣውም ነገር ሁሉ ከንቱ ነው።

9 አንተ ወጣት በወጣትነትህ ጊዜ ደስ ይበልህ፤
በወጣትነትህም ዘመን ልብህ ደስ ያሰኝህ፤
የልብህን መንገድ፣
ዐይንህ የሚያየውንም ሁሉ ተከተል።
ነገር ግን ስለ እነዚህ ነገሮች ሁሉ፣
እግዚአብሔር ወደ ፍርድ እንደሚያመጣህ
ዕወቅ።
10 ስለዚህ ጭንቀትን ከልብህ አርቅ፤
ክፉ ነገርንም ከሰውነትህ አስወግድ፤
ወጣትነትና ጉብዝና ከንቱ ናቸውና።

**12** የጭንቀት ጊዜ ሳይመጣ፣
"ደስ አያሰኙኝም"
የምትላቸው ዓመታት ሳይደርሱ፣
በወጣትነትህ ጊዜ፣
ፈጣሪህን አስብ።
2 ፀሐይና ብርሃን፣
ጨረቃና ከዋክብት ሳይጨልሙ፣
ደመናትም ከዝናብ በኋላ ሳይመለሱ፣
3 ቤት ጠባቂዎች ሲርዱ፣
ብርቱዎች ሲጒብጡ፣
ጥቂት በመሆናቸው ፈጪታዎች ሲያቆሙ፣
በመስኮት የሚያዩትም ሲፈዙ፣
4 ወደ አደባባይ የሚያወጡ በሮች ሲዘጉ፣
ወፍጮ ሚልጦ ድምፁ ሲላሽ፣
ሰው በወፍ ድምፅ ሲነሣ፣
ዝማሬው ሁሉ ሲደክም፣
5 ዳገት መውጣት ሲያርድ፣
መንገድም ሲያስፈራ፣
የለውዝ ዛፍ ሲያብብ፣
አንበጣም ራሱን ሲጐትት፣
ፍላጎት ሲጠፋ፤
በዚያን ጊዜ ሰው ወደ ዘላለማዊ ቤቱ ይሄዳል፤

[1] 5 *ወይም አካል በእናት ማሕፀን ውስጥ እንዴት እንደሚሠራ እንደማታውቅ ሁሉ፣*

10፥19 ዘፍ14፥18፤ መሳ9፥13
10፥20 ዘፀ22፥28
11፥1 ቀኍ6፤ዘዳ 24፥19፤ኢሳ32፥20 ፤ሆሴ10፥12
11፥5 ዮሐ3፥8-10፤ መዝ139፥14-16፤
11፥6 መክ9፥10
11፥7 መክ7፥11
11፥8 መክ12፥1
11፥9 እዮ19፥29፤ መክ2፥24፤3፥17
11፥10 መዝ94፥19፤ መክ2፥24
12፥12 ሳሙ19፥35፤ መክ11፥8
12፥4 ኤር25፥10
12፥5 ኢዮ10፥21፤ ኤር9፥17፤አሞ5፥16

10፥19 *ገንዘብም ካለ ሁሉ ነገር አለ፤* ይህ ዐረፍተ ነገር የተለያየ ትርጒም ሊይዝ ይችላል፤ ይኸውም ስለ ሰው የተሰጠ መጥፎ አስተያየትን፣ ወይም ከረጅም ዕድሜ ይልቅ መልካም ኑሮ እንደሚሻል የተሰጠ ምክርን ወይም ከገንዘብ የሚገኝ ከፍተኛ ጥቅምን የሚያመለክት ይሆናል (ከሉቃ 16፥9 ጋር ያነጻጽሩ)።

11፥1 *እንጀራህን በውሃ ላይ ጣል፤* ሁልጊዜ ላለመጎዳት ጥንቃቄ ማድረግ ብቻ ሳይሆን (ምሳ11፥24 ይመ)፣ አደጋን ተጋፍጠው በባሕር ላይ ንግድ እንደሚጠቀሙ ሰዎች ቈራጥ እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ እንደ ሆነ ያመለክታል።

11፥2 *ሀብትህን ሰባት ቦታ ... ከፍለህ፤* ያልተጠበቀ አደጋ ደርሶብህ የሌሎችን ርዳታ የምትሻበት ጊዜ ሊኖር ስለሚችል፣ ሀብት ባለህ ጊዜ ለተቸገሩት አካፍል።

11፥3-6 *ደመናት ... ዛፍ ... ነፋስን ... ዘርህን፤* ሊሆን ይችላል፤ ወይም ሳይሆን አልቀረም እያልህ አንድን ነገር ያዝ ለቀቅ አታድርግ፤ ከምታውቀውና ልታደርግ ከምትችለው ቦታ ላይ ጀምር፤ ያንተ ድርሻ ወይም ዕውቀት ውሱን መሆኑን አስተውል።

11፥5 *የነፋስን፤* ከዮሐ 3፥8 ጋር ያነጻጽሩ (በሁሉም ጥቅሶች ውስጥ "ነፋስ" እና "መንፈስ" አንድ ዐይነት ትርጒም አላቸው)።

*11፥7-10፤* ሕይወትን እጅግ በጣም በተሟላ ሁኔታ መምራት አስፈላጊ እንደ ሆነ ያሳስባል።

11፥8-10 *ከንቱ፤* በቍ 7-10 ላይ የተጠቀሱት አስደናቂ ስጦታዎች ዐይናችንን እንዳያሳውሩና እንዳያሳስቱን ያስጠነቅቃል፤ ቍ 9 ወደ ትክክለኛው መንገድ ይመራናል።

11፥9 *ወደ ፍርድ፤* 12፥14 እና ማብ ይመ። ከእግዚአብሔር ዘንድ ሽልማት ወይም ቅጣት መኖሩ እያንዳንዱ የሕይወት ጒዞ ዋጋ እንዳለው እንጂ ከንቱ መሆኑን አያመለክትም፤ ይህን ማወቅም ለልባችን ምሪት ይሆናል፤ በዐይናችንም አጥርተን እንድናይ ይረዳናል። ይህ አካሄድ ለም12 የተመቻቸ ሁኔታን ይፈጥራል።

*12፥2-5፤* የሰው የኑሮ ሁኔታ እየተበላሸ እንደሚሄድ የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫ ነው፤ የማርጀትንም ሁኔታ በንጽጽር ያመለክታል።

12፥3 *ቤት ጠባቂዎች፤* ይህ ሐረግና ሌሎች ተለዋጭ ዘይቤዎች የሰውነት ክፍሎችን ሳያመለክቱ አይቀርም። ነገር ግን ምስያውን ለመጠቀም ብቻ ሲባል ጨለማን፣ ማእበልን፣ ሊወድቅ ያዘመመን ቤት፣ ባዶ የቀረ የውሃ ጒድጓድንና የመሳሰሉትን (ቍ5) ዘይቤያዊ አገላለጽ አደናቅፎ የቅኔውን ውበት ማበላሸት አይገባም።

12፥5 *የለውዝ ዛፍ፤* በላዩ ላይ ያለው የገረጣ አበባ ከእርጅና የተነሣ የሚበቅለውን ሽበት ያመለክት ይሆናል። *አንበጣም፤* በተፈጥሮው ፈጣን ነው፤ ቅዝቃዜ ባለበት ማለዳ በዝግታ መንቀሳቀሱም (ከናሆ 3፥17 ጋር ያነጻጽሩ)፣ ሰውነት እንደ ልብ የማይታዘዝበትን የሽምግልና ጊዜ ያመለክታል። *ዘላለማዊ ቤቱ፤*

አልቃሾችም በአደባባዮች ይዞራሉ።

6የብር ሰንሰለት ሳይበጠስ፣
የወርቅ ሳሕንም ሳይሰበር፣
የውሃ መቅጃው በምንጩ አጠገብ
ሳይከሰከስ፣
ወይም መንኰራኵሩ በውሃ ጕድጓድ
ላይ ሳይሰበር፣
7ዐፈር ወደ መጣበት መሬት ሳይመለስ፣
መንፈስም ወደ ሰጠው ወደ እግዚአብሔር
ሳይመለስ፣
ፈጣሪህን አስብ።

8ሰባኪው[ገ] "ከንቱ! ከንቱ!
ሁሉም ነገር ከንቱ ነው!" ይላል።

## የነገሩ ፍጻሜ

9ሰባኪው ጥበበኛ ብቻ አልነበረም፤ ነገር
ግን ለሕዝቡ ዕውቀትንም ያስተምር ነበር።
እርሱም በጥልቅ አሰበ፤ ተመራመረም፤ ብዙ
ምሳሌዎችንም በሥርዐት አዘጋጀ። 10ሰባኪው
ትክክለኛውን ቃል ለማግኘት ተመራመረ፤
የጻፈውም ቅንና እውነት ነበር።
11የጠቢባን ቃላት እንደ ሹል የከብት
መንጃ ናቸው፤ የተሰበሰቡ አባባሎቹም እጅግ
ተቀብቅበው እንደ ገቡ ችንካሮች ሲሆኑ፣
ከአንድ እረኛ የተሰጡ ናቸው። 12ልጄ ሆይ፤
ከዚህ ሁሉ በላይ በማንኛውም ነገር ተጠ
ንቀቅ፤ አንዳችም አትጨምር።
ብዙ መጻሕፍትን መጻፍ ማብቂያ የለውም፤
ብዙ ማጥናትም ሰውነት ያደክማል።

13እንሆ፤ ሁሉ ነገር ከተሰማ ዘንድ፤
የነገሩ ሁሉ ድምዳሜ ይህ ነው፤
እግዚአብሔርን ፍራ፤ ትእዛዛቱንም ጠብቅ፤
ይህ የሰው ሁለንተናዊ ተግባሩ ነውና።
14መልካምም ይሁን ክፉ፣
ስውር የሆነውን ነገር ሁሉ አንድ
ሳይቀር፣
ማንኛውንም ሥራ እግዚአብሔር ወደ
ፍርድ ያመጣዋልና።

[ገ]8 ወይም *የጉባኤ መሪ* እንዲሁም በቍ9 እና 10

12፥7 ዘፍ2፥7፤ ኢዮ20፥8፤መዝ 146፥4፤መክ3፥21፤
12፥8 መክ1፥1:2
12፥9 1ነገ4፥32
12፥10 ምሳ22፥20-21
12፥11 ዕዝ9፥8፤ኢዮ 6፥25
12፥12 መክ1፥18
12፥13 ዘዐ20፥20፤ ዘዳ4፥2:6፤1ሳሙ12፥24፤ኢዮ23፥15፤37፥24
12፥14 ኢዮ19፥29፤ 34፥21፤መዝ19፥12፤ መክ3፥17፤ኤር16፥17፤23፥24

ከምንባቡ አንጻር ይህ የሚያመለክተው መቃብርን እንጂ ከዚያ ባሻገር ያለውን አይደለም።

12፥6 *የብር ሰንሰለት ... የወርቅ ሳሕንም፤* በብር ሰንሰ ለት ተንጠልጥሎ እንደ ተሰቀለ መብራት ማለት ነው፤ ድንገት አንድ ሰው ቢሰብረው፣ ብርሃኑና ውበቱ ይጠፋል፤ የሰውም ሕይ ወት እንደዚሁ ፈጥኖ እንደሚጠፋ ያመለክታል።

12፥8 *ከንቱ፤* ያለ እግዚአብሔር የሆነ ከፀሓይ በታች ያለ ምድራዊ ሕይወት መጨረሻው ምን እንደሚመስል የሚያመለክት ቃል ነው፤ ነገር ግን ወደ ፈጣሪያችን ብንቀርብ (ቍ 1)፣ የእር ሱም ፍርድ እርግጠኛ እንደ ሆነ ብንረዳ (11፥9)፣ ሕይወት ከንቱ አይሆንም። *ሰባኪው፤* የ1፥1 ማብ ይመ።

12፥9 *አሰበ፤ ተመራመረም፤* ሰው እውነትን ለመፈለግና ማስተዋልን ለማግኘት የተቻለውን ሁሉ በማድረግ ያሳየውን ከባድ ጥረት ያመለክታል።

12፥11 *በአንድ እረኛ የተሰጡ፤* በቍ 12 ላይ በአጽንዖት እንደ ተገለጸው የእግዚአብሔር ቃል የራሱ የሆነ የተለየ ሐሳብ እንዳለው በማሳየት የነገሩን ሌላ ገጽታ ያመለክታል።

*12፥13-14፤* ዋናውን የሰው ሕይወት መጨረሻ ያመለክታል።

12፥13 *እግዚአብሔርን ፍራ፤* በፍቅር እግዚአብሔርን ማክ በር የጥበብ መሠረቱ (መዝ 111፥10፤ ምሳ 1፥7፤9፥10)፣ የጥበብ ሁለንተናው (ኢዮ 28፥28) እና መደምደሚያው ነው። *ሰው ማድረግ የሚገባው ሁሉ፤* ከንቱ ከመሆን ለመዳን አስቀድመን ማድረግ የሚገባንን ዐቢይ ጕዳይ የሚያመለክት ማለት ነው።

12፥14 *ማንኛውንም ሥራ ... ወደ ፍርድ፤* የዚህ እውነት ፍንጭ ዐልፎ ዐልፎ በመጽሐፉ ውስጥ በ3፥17፤ 8፥12-13፤ 11፥9 እና በማብራሪያው ላይ ተጠቅሶአል፤ ማቴ 12፥36፤ 1ቆሮ 3፥12-15፤ 2ቆሮ 5፥9-10፤ ዕብ 4፥12-13 ይመ። *ስውር የሆነውን ነገር ሁሉ፤* ሮሜ 2፥16 ይመ።